# የብልፅግና ፓርቲ

# የአደረጃጀትና የአሠራር መመሪያ ቁጥር 24/2017

**(የፀደቀ)**

ነሐሴ 15 ቀን 2017 ዓ.ም

አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ

መግቢያ 1
ክፍል አንድ ........ 2
ጠቅላላ ድንጋጌዎች 2
1. አጭር ርዕስ ........ 2
2. ትርጓሜ ........ 2
3. የመመሪያው ዓላማ ........ 4
4. የመመሪያው የተፈጻሚነት ወሰን ........ 4
ክፍል ሁለት ........ 5
የብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽ/ቤትና የፌዴራል ተቋማት አደረጃጀት፣ ተግባራት፣ ኃላፊነቶችና አሰራር 5
5. የብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽ/ቤት አደረጃጀት፤ ........ 5
6. የፓርቲ ዋና ጽ/ቤት ........ 5
7. የፓርቲ ዋና ጽ/ቤት ኃላፊ........ 6
8. የብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽ/ቤት የሥራ አመራር ኮሚቴ አደረጃጀት........ 7
9. የብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽ/ቤት ሥራ አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት ........ 8
10. የብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽ/ቤት ሥራ አመራር ኮሚቴ አሰራር ........ 9
11. የብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽ/ቤት ዘርፎች አደረጃጀት ........ 9
12. የፌዴራል ተቋማት አስተባባሪ አደረጃጀት ........ 24
13. የፌዴራል ተቋማት አስተባባሪ ኮሚቴ ተግባራትና ኃላፊነቶች ........ 25
14. የፌደራል ተቋማት አስተባባሪ ኮሚቴ አሰራር........ 26
15. የፌዴራል ተቋማት ክላስተር አመራር ኮሚቴ አደረጃጀት........ 26
16. የፌዴራል ተቋማት ክላስተር ተግባርና ኃላፊነት ........ 26
17. የፌዴራል ተቋማት ክላስተር አመራር ኮሚቴ አሰራር ........ 27
18. የፌዴራል ተቋማት ወረዳ አመራር አደረጃጀት ........ 28
19. የፌዴራል ተቋማት ወረዳ አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት........ 28
20. የወረዳ አመራር ኮሚቴ አሰራር ........ 29
ክፍል ሦስት........ 30
በክልል፣ በዞን፣ በወረዳና በቀበሌ የፓርቲ አደረጃጀት፣ ተግባራት፣ ኃላፊነቶችና አሰራር 30
21. የክልል አመራር አካላት አደረጃጀት፣........ 30
22. በክልል የአስተባባሪ ኮሚቴ አደረጃጀት........ 30
23. በክልል የአስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት ........ 30
24. በክልል የአስተባባሪ ኮሚቴ አሰራር ........ 32
25. በክልል የብልፅግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥራ አመራር ኮሚቴ አደረጃጀት........ 32
26. በክልል የብልፅግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥራ አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት ........ 32

27. በክልል የብልፅግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥራ አመራር ኮሚቴ አሰራር ..... 34
28. በዞን የአመራር አካላት አደረጃጀት ..... 34
29. በዞን የአስተባባሪ ኮሚቴ አደረጃጀት ..... 35
30. በዞን የአስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት ..... 35
31. በዞኑ የአስተባባሪ ኮሚቴ አሰራር ..... 36
32. በዞን የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥራ አመራር ኮሚቴ አደረጃጀት ..... 36
33. በዞን የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥራ አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት ..... 37
34. በዞን የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥራ አመራር ኮሚቴ አሰራር ..... 38
35. በወረዳ የአመራር አካላት አደረጃጀት ..... 39
36. በወረዳ የአስተባባሪ ኮሚቴ አደረጃጀት ..... 39
37. በወረዳ የአስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት ..... 39
38. በወረዳ የአስተባባሪ ኮሚቴ አሰራር ..... 40
39. በወረዳ የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥራ አመራር ኮሚቴ አደረጃጀት ..... 41
40. በወረዳ የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ስራ አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት ..... 41
41. በወረዳ የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ አሰራር ..... 43
42. በቀበሌ የአመራር አካላት አደረጃጀት ..... 43
43. በቀበሌ የአስተባባሪ ኮሚቴ አደረጃጀት ..... 43
44. በቀበሌው የአስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት ..... 44
45. በቀበሌ የአስተባባሪ ኮሚቴ አሰራር ..... 45
46. በቀበሌ የብልፅግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥራ አመራር ኮሚቴ አደረጃጀት ..... 45
47. በቀበሌው የብልፅግና ፓርቲ ቅ/ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት ..... 45
48. በቀበሌው የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ አሰራር ..... 46

**ክፍል አራት** ..... 48

**የብልፅግና ህብረት፣ የብልፅግና ቤተሰብና የፓርቲ ደጋፊ አባልና ግለሰብ አደረጃጀት፣ ተግባርና ኃላፊነትና አሠራር** 48

49. የብልፅግና ህብረት አደረጃጀት ..... 48
50. የብልፅግና ህብረት የአመራር ኮሚቴ ..... 49
51. የብልፅግና ህብረት አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት ..... 50
52. የብልፅግና ህብረት ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት ..... 52
53. የብልፅግና ህብረት ፖለቲካ ሥራዎች ሃላፊ ተግባርና ኃላፊነት ..... 52
54. የብልፅግና ህብረት አደረጃጀት ሥራዎች ኃላፊ ተግባርና ኃላፊነት ..... 52
55. የብልፅግና ህብረት ፋይናንስ ሥራዎች ኃላፊ ተግባርና ኃላፊነት፣ ..... 53
56. የፖለቲካ ሥራዎች ንኡስ ኮሚቴ አመራር አባላት አደረጃጀት ..... 53

57. የአደረጃጀት ሥራዎች የንኡስ ኮሚቴ አደረጃጀት ........ 54
58. የብልፅግና ህብረት የፋይናንስ ሥራዎች ንኡስ ኮሚቴ ........ 55
59. የብልፅግና ህብረት አሰራር ........ 55
60. የብልፅግና ቤተሰብ አደረጃጀት ........ 56
61. የብልፅግና ቤተሰብ አመራር ኮሚቴ ........ 58
62. የብልፅግና ቤተሰብ አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት ........ 58
63. የብልፅግና ቤተሰብ ሰብሳቢ የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል። ........ 59
65. የአደረጃጀት ጉዳይ ኃላፊ የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል። ........ 60
66. የብልፅግና ቤተሰብ ገንዘብ ያዥ የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል። ........ 60
67. የብልፅግና ቤተሰብ አሰራር ........ 61
68. ሁለት ኃላፊነት መያዝ የተከለከለ ስለመሆኑ ........ 61
69. የፓርቲ ደጋፊ አባላት አደረጃጀት ........ 61
70. የፓርቲ ደጋፊ አባላት አደረጃጀት ተግባርና ኃላፊነት ........ 61
71. የፓርቲ ደጋፊ አባላት አደረጃጀት አሰራር ........ 62
72. የፓርቲ ደጋፊ ግለሰቦች አደረጃጀት ........ 62
73. የፓርቲ ደጋፊ ግለሰቦች አደረጃጀት ተግባርና ኃላፊነት ........ 63
74. የፓርቲ ደጋፊ ግለሰቦች አደረጃጀት አሰራር ........ 63
**ክፍል አምስት** ........ 64
**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች** 64
75. በየክልሉ የሚገኙ የፌዴራል መንግስት ተቋማት አባላት አደረጃጀት ........ 64
76. በየደረጃው የሚኖር የፓርቲ ኮንፈረንስ ውክልና ........ 64
77. መመሪያውን ስለማስፈጸም ........ 64
78. ግንዛቤ ስለመፍጠር ........ 64
79. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች ........ 65
80. መመሪውን ስለማሻሻል፣ ........ 65
81. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ ........ 65

## መግቢያ

በብልፅግና ፓርቲ ሁለተኛ መደበኛ ጉባዔ ተሻሽሎ የጸደቀ መተዳደሪያ ደንብ አዳዲስ ድንጋጌዎች የተካተቱ በመሆናቸው በሥራ ላይ የነበረውን የብልፅግና ፓርቲ የአባላትና የአመራር አካላት አደረጃጀት፣ ተልዕኮና አሰራር ጊዜያዊ መመሪያ ማሻሻል በማስፈለጉ፣

ጊዜያዊ መመሪያው በሥራ ላይ በዋላባቸው ዓመታት በሥራ ውስጥ የታዩ ክፍተቶች እና በመመሪያው ያልተሸፈኑ ጉዳዮች መኖራቸው በመረጋገጡ ፣

የፓርቲውን አደረጃጀቶችና አካላትን አመሰራረት፣ ተግባርና ኃላፊነት፣ አሰራር፣ የግንኙነት አግባቦች ወጥነት፣ ግልፅነትና ተጠያቂነትን በሚያረጋግጥ መልኩ መዘርጋት በማስፈለጉ፤

የዋና ጽህፈት ቤትና በየደረጃው የክልል ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶችን ዝርዝር አሰራርን አስመልክቶ ለምክር ቤት እንደሚያቀርብ በመተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 5 በግልጽ በመደንገጉ፣

የብልፅግና ፓርቲ ምክር ቤት በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 42 በተሠጠው ስልጣን መሠረት ይህ መመሪያ ወጥቷል።

# ክፍል አንድ
# ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ **"የብልፅግና ፓርቲ የአደረጃጀትና የአሰራር መመሪያ ቁጥር** 24/2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 2. ትርጓሜ

**የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-**

1) **"ፓርቲ"** ማለት ብልፅግና ፓርቲ /ብልፅግና/ ማለት ነው።
2) **"ጉባኤ"** ማለት የፓርቲው ከፍተኛ አመራር አካል ነው።
3) **"ፕሮግራም"** ማለት የፓርቲው አንደኛው መደበኛ ጉባኤ የፀደቀው የፓርቲ ፕሮግራም ነው።
4) **"መተዳደሪያ-ደንብ"** ማለት በፓርቲው ሁለተኛ መደበኛ ጉባኤ የፀደቀው የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ ማለት ነው፣
5) **"የብልፅግና ምክር ቤት"** ማለት በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ከጉባኤ እስከ ጉባኤ ፓርቲውን የሚመራ ከፍተኛ የብልፅግና ፓርቲ አካል ነው፤
6) **"ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ"** ማለት በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ከብልፅግና ምክር ቤት አባላት መካከል የሚመረጡ የፓርቲ ጉባዔና በብልፅግና ፓርቲ ምክር ቤት የተወሰኑ ውሳኔዎችን አስፈፃሚ አካል ነው።
7) **"ኮሚሽን"** ማለት በፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ የተቋቋመ በየደረጃው የሚገኘው የፓርቲው ኢንስፔክሽንና ሥነ-ምግባር ኮሚሽን ማለት ነው፤
8) **"አመራር"** ማለት የብልፅግና ፓርቲ አባላት የሆኑ እና በፓርቲው አማካኝነት በመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ በፓርቲው ጽህፈት ቤቶች እና በልዩ ልዩ የአመራርነት ቦታዎች በምርጫ ፣በሹመት ወይም በምደባ ኃላፊነት የተሰጣቸው የፓርቲ አባላት ናቸው።
9) **"አስተባባሪ ኮሚቴ"** ማለት የፓርቲና የመንግስት ሥራዎችን አቀናጅቶ በበላይነት የሚያስተባብር እና በፓርቲው የበላይ አካላት የሚተላለፉ ውሳኔዎችና መመሪያዎች በተግባር ላይ መዋላቸውን የሚያረጋግጥ በየደረጃው የሚገኝ የፓርቲው አደረጃጀት ነው።
10) **"የሥራ አመራር ኮሚቴ"** ማለት የፓርቲ ዋና ጽ/ቤትና በየደረጃዉ በሚገኙ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በዚህ መመሪያ የተሰጣቸውን ተግባራትን በአግባቡ ተግባራዊ መሆናቸውን የሚከታተል አካል ነው።

11) **"ምዘና"** ማለት የፓርቲው አመራርና አባላት በመደበኛ ሥራዎችና በውስጠ-ፓርቲ ተልዕኮዎች፣ አደረጃጀቶች በውስጠ-ፓርቲ ተልዕኮ አፈፃፀም ግልጽ በሆነ መመዘኛ መሰረት በውጤት ተኮር የሚለካበትና ውጤት የሚሰጥበት ሂደት ማለት ነው።

12) **"ዋና ጽህፈት ቤት"** ማለት የብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽህፈት ቤት ነው።

13) **"ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት"** ማለት ከክልል እስከ ቀበሌ ባሉ መዋቅሮች የተቋቋመ የብልፅግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ማለት ነው።

14) **"ዘርፍ"** ማለት በብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽ/ቤትና በየደረጃዉ በሚገኙ የብልፅግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በዚህ መመሪያ የተሰጣቸውን ተግባራትና ኃላፊነቶችን በአግባቡ ለመተግበር እንዲቻል የተፈጠሩ አደረጃጀቶች ናቸው።

15) **"ክልል"** ማለት በህገ-መንግሥቱ አንቀጽ 47 መሠረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ አስተዳደርን ይጨምራል።

16) **"የፌዴራል ተቋማት"** ማለት ለፌዴራል መንግስት ተጠሪ የሆኑ የመንግሥት እና የመንግሥት ልማት ድርጅቶችን ያጠቃልላል።

17) **"ዞን"** ማለት ለክልል ተጠሪ የሆኑ የዞን አስተዳደር፣ የአዲስ አበባ ክፍለ ከተሞች እና በዞን ደረጃ ያሉ ከተሞችን፣ በዞን ደረጃ ያሉ ክፍለ ከተሞችን እና ልዩ ወረዳዎችን የሚያጠቃልል ነው።

18) **"ወረዳ"** ማለት በክልሎች፣ በአዲስ አበባ ከተማና በሸገር ከተማ ወረዳ እና በድሬዳዋ አስተዳደር የከተማ ቀበሌና ገጠር ክላስተር አካላትን ያጠቃልላል።

19) **"ቀበሌ"** ማለት የከተማና የገጠር ቀበሌዎችን የሚያጠቃልል ይሆናል።

20) **"ከተማ"** ማለት በከተማ ልማት የከተማ ደረጃ የተሰጣቸውንና በከንቲባ የሚመሩ ሁሉ የሚያጠቃልል ነው።

21) **"የክልል ርዕሰ-መስተዳድር ወይም ፕሬዝዳንት"** ማለት የክልሎች ርዕሳነ-መስተዳድሮች ወይም ፕሬዝዳንቶች እና ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል የአዲስ አበባ ከተማና የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባዎችን ያጠቃልላል።

22) **"የክልል ምክትል ርዕሰ-መስተዳድር ወይም ምክትል ፕሬዝዳንት ደረጃ የሚገኙ"** ማለት የክልል ምክትል ርዕሰ-መስተዳድር ወይም ምክትል ፕሬዝዳንት ደረጃ የሚገኙ አመራሮች እና ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም ሲባል የአዲስ አበባና ድሬዳዋ ምክትል ከንቲባና በምክትል ከንቲባ ደረጃ ያሉትን ያጠቃልላል።

23) **"የብልፅግና ህብረት"** ማለት በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የተቋቋመና ሁለት እና ከዚያ በላይ የብልፅግና ቤተሰብን ያቀፈ ማለት ነው።

24) **“የብልፅግና ቤተሰብ”** ማለት በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የተቋቋመና የአባላት የዕለት ተዕለት አቅም የሚገነባበት የፓርቲው የመጨረሻው እርከን የአባላት ስብስብ አደረጃጀት ነው።

25) **”ኮንፈረንስ“** ማለት በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የተቋቋመና በየደረጃው የፓርቲ አባላት በጋራ ሆነው የተግባራት አፈጻጸም ግምገማና የተለያዩ ውሳኔዎችን የሚያስተላልፉበት መድረክ ነው።

26) **“ ክላስተር“ ማለት** ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ የሆኑትን ተቋማት በማቀናጀት የፓርቲውን ተልዕኮ ለማሳካት የተፈጠረ አደረጃጀት ነው።

27) “ የፓርቲ **ደጋፊ ግለሰቦች አደረጃጀት“ ማለት** በግለሰብ ደረጃ ፓርቲውን በተለያ መንገድ በእውቀት ፣በገንዘብ እና በሙያ የሚደግፉ ግለሰቦች ስብስብ ማለት ነው።

28) **“ የፓርቲ ደጋፊ አባላት አደረጃጀት“ ማለት** በዕቅድ በመመራት ለፓርቲ አባልነት የተለዩ ወይም በራሳቸው የፓርቲ አባል ለመሆን ጥያቄ ያቀረቡ ግለሰቦች የፖለቲካ አቅም ለመገንባት የሚፈጠር አደረጃጀት ነው።

29) **“ክንፍ”** ማለት የፓርቲው የሴቶችና የወጣቶች አደረጃጀት የወል መጠሪያ ማለት ነው።

30) በዚህ መመሪያ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው ሴትንም ይጨምራል።

## 3. የመመሪያው ዓላማ

በየደረጃው የሚገኙ የፓርቲው ጽ/ቤቶች፣ አደረጃጀቶችና አካላት አመሠራረት፣ ተግባራትና ኃላፊነቶችን፣ አሠራሮችን በግልፅነትና ተጠያቂነት ባለው መልኩ በማስቀመጥ ጠንካራ እና ተጽዕኖ መፍጠር የሚችሉ ጠንካራ ተቋማዊ የፓርቲ አደረጃጀት ለመፍጠር ያለመ ነው።

## 4. የመመሪያው የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በማንኛውም ደረጃ በሚገኙ የፓርቲ አካላት፣ አመራርና አባላት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

# ክፍል ሁለት

# የብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽ/ቤትና የፌዴራል ተቋማት አደረጃጀት፣ ተግባራት፣ ኃላፊነቶችና አሰራር

## 5. የብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽ/ቤት አደረጃጀት፤

1) የብልፅግና ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 26 (6) ለብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽ/ቤት የተሠጡ ተግባራትና ኃላፊነቶች በአግባቡ ለመወጣት እንዲቻል እንደሚከተለው ተደራጅቷል።

ሀ. የፓርቲ ዋና ጽ/ቤት

ለ. የፓርቲ ዋና ጽ/ቤት ኃላፊ

ሐ. የፓርቲ ዋና ጽ/ቤት የሥራ አመራር ኮሚቴ

## 6. የፓርቲ ዋና ጽ/ቤት

1) የፓርቲ ዋና ጽ/ቤት በመተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 26(6) ስር የተዘረዘሩ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) የፓርቲው ብልፅግና ምክር ቤት እና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ዕቅዶችንና ሌሎች በፓርቲው ፕሬዝዳንት የሚሰጡ አቅጣጫዎችን መሠረት በማድረግ የፓርቲውን ሥራዎች ያቅዳል፣ ያስፈጽማል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

ለ) የፓርቲውን ገንዘብ፣ ንብረት እና ሰነዶች በበላይነት ያስተዳድራል፣ በጥንቃቄ እንዲያዙ እና በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣ የፓርቲውን የሂሳብ መዛግብት እና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በየዓመቱ በውጪ የሂሳብ ባለሞያ ወይም ኦዲተር እንዲመረመሩ እና እንዲረጋገጡ ያደርጋል፤

ሐ) የአባላት አደረጃጀት፣ የፖለቲካ ግንባታ፣ የሕዝብና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ የጥናትና ምርምርና ሌሎች ተግባሮችን ይፈፅማል፤

መ) በፓርቲው ፕሬዝዳንት በሚሰጠው አቅጣጫ መሠረት ፓርቲውን ወክሎ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር የሥራ ግንኙነት ያደረጋል፤

ሠ) ከፓርቲው ፕሬዝዳንት ጋር በመመካከር የፓርቲውን ልሳን ዋና አዘጋጅ እና የቦርድ አባላትን ይሰይማል፤

ረ) የጸደቀውን የፓርቲ በጀት ያስተዳድራል፤

ሰ) የፓርቲውን ፕሮግራም፣ አቅጣጫዎች፣ የሥራ አፈጻጸም እና ዕቅዶችን በሚዲያና በሕዝብ ግንኙነት መሣሪያዎች ለሕዝብ ያስተዋውቃል፤

ሸ) በፓርቲው ስም ውል ይዋዋላል፤ ይከሳል፤ ይከሰሳል፤

ቀ) በፓርቲው የሰው ኃይል አስተዳደር መመሪያ መሠረት የጽሕፈት ቤቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤

በ) የፓርቲ ጉባኤ ቦታ፣ ጊዜና አጀንዳ አዘጋጅቶ ሲወሰን ለሚመለከተው ፓርቲ አደረጃጀት ያሳውቃል፤

ተ) የፓርቲው አሰላሳይ ቡድን ሥራዎችን ያስተባብራል፤

ቸ) በብልፅግና ምክር ቤት፣ በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ወይም በፕሬዝዳንቱ የሚሰጡ ሌሎች ሥራዎችን ያከናውናል።

በ) ጽ/ቤቱ ተጠሪነቱ ለፓርቲ ፕሬዝዳንቱ ይሆናል።

2) በመተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 31 መሰረት የተቀመጡ ተግባራትና ኃላፊነቶች በየደረጃው የሚገኙ የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ይኖረቸዋል።

## 7. የፓርቲ ዋና ጽ/ቤት ኃላፊ

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6(1) መሠረት የፓርቲ ዋና ጽ/ቤት የተሰጡ ተግባራትና ኃላፊነቶችን ያስፈጽማል፣

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የፓርቲ ዋና ጽ/ቤት ኃላፊ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖረዋል፣

ሀ) የፓርቲ ዋና ጽ/ቤት የዘርፍ ኃላፊዎች እና ምክትል ዘርፍ ኃላፊዎች ከፓርቲው ፕሬዝዳንት እና ምክትል ፕሬዝዳንት ጋር በመነጋገር ይመድባል፣ያሰናብታል፣

ለ) የክልል ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊዎችን ከፓርቲው ፕሬዝዳንት፣ ምክትል ፕሬዝዳንት እና ከክልል አስተባባሪ ኮሚቴ ጋር በመነጋገር ይመድባል፣ያሰናብታል፣

ሐ) የፓርቲ ዋና ጽ/ቤት በጸደቀው መዋቅር መሠረት ዳይሬክተሮችንና አስፈላጊ ኃላፊዎችን ከዘርፍ ኃላፊዎች ጋር በመመካከር ይመድባል፣ ያሰናብታል፣

መ) ለፓርቲ ዋና ጽ/ቤት ተጠሪ የሆኑ አካላትን የሥራ ስምሪት ይሰጣል፣

ሠ) በብልፅግና ፓርቲ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እና የብልፅግና ምክር ቤት የሚሰጡ ውሳኔዎችና አቅጣጫዎች አፈፃፀም ይከታተላል፣ ይደግፋል፣

ረ) ጽ/ቤቱን ወክሎ ከሦስተኛው ወገኖች ጋር የሥራ ግንኙነት ያደርጋል፣

ሰ) የፓርቲው ሀብቶች በአሠራር መመሪያዎች መሰረት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፣

ሸ) የፓርቲ ዋና ጽ/ቤት የሥራ አመራር ኮሚቴ እና የክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የጋራ የግምገማ መድረክ ስብሰባዎችን ይመራል፣ ያስተባብራል፣

ቀ) የሥራ አመራር ኮሚቴው በዚህ መመሪያ መሠረት መሥራቱን ይቆጣጠራል፣

በ) ለሥራ አመራር ኮሚቴ የስብሰባ አጀንዳ በመቅረጽና በማቅረብ ያጸድቃል፣

ተ) በሥራ አመራር ኮሚቴ ስብሰባ ላይ ቀርበው ማብራሪያ እንዲሰጡ የሚፈለጉ የሥራ ኃላፊዎችን ወይም ባለሙያዎችን እና ሌሎች ግለሰቦችን በሥራ አመራር ኮሚቴ ስብሰባ ላይ እንዲገኙ ይፈቅዳል፣

ቸ) ለሥራ አመራር ኮሚቴ የቀረበ ጉዳይ በሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም አሰላሳይ ቡድን ወይም በሌላ ኮሚቴ መታየት የሚያስፈልገው ሆኖ ካገኘው በሌላ ጊዜ እንዲታይ ያደርጋል፣

ኀ) የሥራ አመራር ኮሚቴው በተወያየባቸው ጉዳዮች ላይ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በፓርቲው ውሳኔ አሰጣጥ ስርዓት ድምጽ እንዲሰጥ ያደርጋል፣

ነ) የፓርቲው መሰረታዊ ሰነዶች የድምጽ፤ የምስልና የጽሁፍ (ሃርድ እና ሶፍት ኮፒ) በጥንቃቄና በዘመናዊ መንገድ እንዲያዙ ያደርጋል፤ የብልፅግና ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እና የብልፅግና ምክር ቤት እንዲሁም የፓርቲውን የጉባኤ ሪፖርቶችና ቃለ ጉባኤዎች በአግባቡ ተደራጅተው እንዲያዙ ያደርጋል፤ በየዓመቱ ስራ ላይ የዋሉ እቅዶች፤ ግምገማዎች፤ ከተለያዩ አካላት ጋር የተደረጉ ግንኙነቶች በሰነድነት እንዲያዙ ያደርጋል፤

ኘ) የህግ አገልግሎትና ኦዲት አገልግሎት ክፍሎች ይከታተላል፣

አ) የሥራ አመራር ኮሚቴ ውሳኔዎችና አቅጣጫዎች ተግባራዊነት ይከታተላል፣

ከ) ጽ/ቤት ሃላፊው ተጠሪነቱ ለፓርቲ ፕሬዝዳንቱ ነው።

3) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6(2) ለፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና በዚህ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (2) ለፓርቲ ዋና ጽ/ቤት ሃላፊ የተሰጡት ተግባራትና ኃላፊነቶች በየደረጃው ለሚገኙ የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊዎች ይሆናል።

## 8. የብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽ/ቤት የሥራ አመራር ኮሚቴ አደረጃጀት

ሀ) የብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽ/ቤት የሥራ አመራር ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለፓርቲ ጽ/ቤት ሃላፊ ነው።

ለ) ሁሉም የዘርፍ ሃላፊዎችንና ምክትል ዘርፍ ሃላፊዎች የስራ አመራር ኮሚቴ አባላት ይሆናሉ።

ሐ) በፓርቲ ዋና ጽ/ቤት የወጣቶችና ሴቶች ክንፍ ጽ/ቤት ሃላፊዎች.............ያለድምጽ

መ) የፓርቲ ዋና ጽ/ቤት ልዩ ረዳት ቃለ ጉባዔ ያዥ...............................ያለድምጽ

## 9. የብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽ/ቤት ሥራ አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. የብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽ/ቤትን የብልፅግና ፓርቲን ዓመታዊ እቅድ ያጸድቃል፣ ለሚመለከታቸው አካላት የዕቅድ ኦሬንቴሽን ይሰጣል፣ አፈፃፀሙም ይከታተላል፣ ይደግፋል፤
2. የብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽ/ቤትን የየዘርፎች ዕቅድ ያዳምጣል፣ ያጸድቃል፣ አፈጻጸም ሪፖርት ያዳምጣል፣ ይገመግማል፣ አቅጣጫ ይሰጣል፣
3. የፓርቲውን የአባላትና የአመራር የስልጠና እቅድ ተወያይቶ ያጸድቃል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ አቅጣጫ ይሰጣል፣ ይደግፋል፣
4. የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ፣ መመሪያዎች፣ የጉባዔ እና የብልፅግና ፓርቲ ምክር ቤት ውሳኔዎችና አቅጣጫዎችን ሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፤ በአፈጻጸም የሚያጋጥሙትን ችግሮችን በመለየት የመፍትሄ አቅጣጫ ይሰጣል፣
5. የፓርቲ የገንዘብና ንብረት የውስጥና በውጭ ኦዲተር ኦዲት ግኝቶች ላይ ይወያያል፣ አቅጣጫ ይሰጣል፣ ኦዲት ያስደርጋል፣ ተጠያቂነትን ያሰፍናል፤
6. የፓርቲውን ጽ/ቤት መዋቅር ተጠንቶ ሲቀርብ ያጸድቃል፣
7. የፓርቲው ፖለቲካዊ ጥራትና የሥነ-ምግባር ጤናማነት በየደረጃው እንዲረጋገጥ ስልቶችን ይቀይሳል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣ አፈጻጸሙን በመገምገም አቅጣጫ ይሰጣል፣
8. የውስጠ-ፓርቲ ዴሞክራሲ እንዲጎለብት በየደረጃው የሚደረጉ ውይይቶች፣ ግምገማዎችና ምክክር የአባላት ተሳትፎ መረጋገጡን ይከታተላል፣ የአባላትን ነጻ ተሳትፎ የሚገድቡ ድርጊቶችን ተከስተው ሲገኙ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፣
9. መተዳደሪያ ደንብ፣ መመሪዎች እና አሰራሮች ስራ ላይ መወላቸው እንዲሁም ሌብነትና ብልሹ አሰራሮች በየደረጃው በሚገኙ የፓርቲ አደረጃጀቶች፣ አካላትና አባላት ውስጥ ተቋማዊ በሆነ መልኩ የእቅድና የሪፖርት አካል ሆኖ ትግል እንዲደረግ ያደርጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ ይደግፋል፤ ጥፋቶች ሲፈጸሙ አስተማሪ የእርምት እርምጃዎች እንዲወሰድ ያደርጋል፣
10. ከፓርቲ ኮሚሽን የሚሰጡ የኢንስፔክሽን ግኝቶች፣ ምክረ-ሐሳቦችና ውሳኔዎች በመውሰድ ተገቢነቱን መርምሮ በየደረጃው በሚገኙ የፓርቲ መዋቅር ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፣ ይደግፋል፣
11. የክልል የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ዕቅድና የሥራ አፈጻጸም ይገመግማል፣ አቅጣጫ ይሰጣል፣

12. በየወቅቱ የሚኖሩ ሀገራዊ፣ ቀጣናዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፍ የፖለቲካ አውድ አዝማሚያዎችን እየገመገመ ይሄዳል፣ አቅጣጫዎች ያስቀምጣል፣
13. የጽ/ቤቱን ረቂቅ በጀት ላይ ተወያይቶ እንዲጸድቅ ለሚመለከተው አካል እንዲቀርብ ያደርጋል፣ ሲጸድቅ ያስተዳድራል፣
14. የፓርቲ ሥራዎች የሱፐርቪዥን ግኝቶች ላይ ይወያያል፣ አቅጣጫ ይሰጣል፣

## 10. የብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽ/ቤት ሥራ አመራር ኮሚቴ አሰራር

1. በየአስራ አምስት ቀኑ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣
2. ምልዓተ ጉባዔው 50%+1 ነው።
3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምፅ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50%+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካል ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል። እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል።
4. በፓርቲ ዋና ጽ/ቤት እቅድ እና አፈጻጸም ይገመግማል፣ በጽ/ቤቱ ውስጥ ከሚገኙ ከመላው ተሿሚዎችና ዳይሬክተሮች ጋር በየሦስት ወሩ የጋራ የውይይት መድረክ ይካሄዳል።
5. የፓርቲ ዋና ጽ/ቤት እና የክልል ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እንዲሁም በጽ/ቤቱ ውስጥ ከሚገኙ ከመላው ተሿሚዎችና ዳይሬክተሮች ጋር በየሦስት ወሩ በእቅድ አፈጻጸም ግምገማ የጋራ የውይይት መድረክ ያካሂዳሉ።

## 11. የብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽ/ቤት ዘርፎች አደረጃጀት

**1) የፓርቲው ዋና ጽ/ቤት በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 26 (1) እና (6) በተደነገገው መሠረት የተሠጡትን ተግባራትና ኃላፊነቶች በአግባቡ ለመወጣት እንዲቻል የሚከተሉት ዘርፍች ይኖሩታል።**

ሀ) የፖለቲካና አቅም ግንባታ ዘርፍ፣
ለ) የአደረጃጀት ዘርፍ፣
ሐ) የዴሞክራሲ ባህል ግንባታ ዘርፍ፣
መ) የህዝብና አለም አቀፍ ግንኙነት ዘርፍ፣
ሠ) የጥናትና ምርምር ዘርፍ፣
ረ) የስትራቴጂክ ስራ አመራርና ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍ እና
ሰ) የሀብት አስተዳደር ዘርፍ ናቸው።

**2) በፓርቲ ዋና ጽ/ቤት ሥር የተደራጁ ዘርፎች የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖራቸዋል።**

### ሀ) የፖለቲካና አቅም ግንባታ ዘርፍ፡-

1. ተጠሪነቱ ለፓርቲው ዋና ጽ/ቤት ኃላፊ ይሆናል፤
2. ዘርፉን በበላይነትና በሃላፊነት ይመራል፤
3. ከፓርቲ ዋና ጽ/ቤት እቅድ በመነሳት የዘርፉን ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ሲጸድቅ፣ ይፈፅማል፣ ያስፈፅማል፣ አፈፃፀሙን ይገመግማል፤
4. የዘርፉ ሥራዎች በአግባቡ እንዲከናወኑ ለሥራ ክፍሎች አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤ ያስተባብራል፤ ይከታተላል፤ በዘርፉ ስሩ ያሉትን ምክትል ዘርፍ ኃላፊዎችና ዳይሬክቶሬቶች ይከታተላል፣ ይደግፋል፣ የሥራ አፈፃፀም ይገመግማል፣ ግብረ-መልስ ይሰጣል፣ ይመዝናል፣
5. የፓርቲ ፕሮግራም፣ ማኒፌስቶ፣ እሳቤዎች፣ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና እቅዶች በፓርቲው አመራሮችና አባላት ዘንድ እንዲሰርጹ እንዲሁም ህዝብ እንዲገነዘባቸዉ ያደርጋል፤
6. የፓርቲዉን የአመራር ልማት ፖሊሲ መነሻ በማድረግ የቅድመ ስልጠና ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት እንዲካሄድ ያደርጋል፤ የፓርቲዉ የአመራሮችና አባላት ስልጠና ክፍተቶችና ፍላጎቶች ይለያል፣ ውጤታማ ስልጠና እንዲሰጥ ያስተባብራል፤
7. የስልጠናዎች ውጤታማነት ለማረጋጋጥ የድህረ ዳሰሳ ጥናት እንዲካሄድ በማድረግ ግኝቶችን ያቀርባል፣ ለቀጣይ ስልጠናዎች በግብዓትነት ይጠቀማል፤
8. በየጊዜው የሚካሄዱ ሀገራዊና አካባቢያዊ ምርጫዎችን በአሸናፊነት ለመወጣት የሚያስችል የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞችን በመቅረጽና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ለአባላት የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን ይሰጣል፤
9. የፓርቲ አመራርና አባላት የፖለቲካ ጥራት የአስተሳሰብና የተግባር አንድነት ለመፍጠር እና መልካም ሥነ-ምግባር ለማዳበር የሚረዱ ልሳነ-ብልፅግና እና ሌሎች የፖለቲካ ሰነዶችን በማዘጋጀት በየደረጃው በኮንፈረንስ፣ በዎርክሾፕ፣ በፓናል በሴሚናሮችና በስልጠና መድረኮች ውይይት እንዲደረግባቸው ያደርጋል፣ ክትትል፣ ድጋፍ እና ግብረ-መልስ ይሰጣል፤
10. ሌብነትንና ብልሹ አሰራርን በአስተሳሰብና በተግባር የሚጸየፍ በመሰረታዊነት ለውጥ ሊያመጣና ለትግል የሚያዘጋጅ የአቅም ግንባታ ስልጠና ይሰጣል፣
11. ፓርቲው በፕሮግራሙ፣ ማኒፌስቶው፣ በፓርቲዉ የበላይ አካል የሚተላለፉ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና የዲፕሎማሲ አቅጣጫዎች እየተፈጸሙበት ያለበትን ሁኔታ በመከታተል፤ በመረዳትና በመተንተን ምክረ ሀሳብ ለበላይ አካል ያቀርባል፤

12. የህዝብ ምክክር፣ የፖለቲካ አስተምህሮትና ንቅናቄ መድረኮችን ያዘጋጃል፣ ተግባራዊነቱን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣

13. ዓለማዊ፣ ቀጠናዊና የሀገሪቱን ወቅታዊ የፖለቲካዊ ሁኔታዎችን በጥልቅ መረጃዎች ላይ ተመርኩዞ በመገምገም፣ የሁኔታ ትንታኔ በመስራት ለበላይ አካል ያቀርባል፣

14. የፓርቲውን አንድነት፣ ጥራትና ጥንካሬ፣ ኅብረ ብሔራዊ አንድነትን፣ የወንድማማችነትና እህትማማችነትን እሴት ለመገንባት የሚያስችሉ የፖለቲካ ሥራዎች ይሰራል፣ ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣

15. ወንድማማችነትና እህትማማችነትን ለማጠናከር፣ ሀገራዊ መግባባትን የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ፣ ማህበራዊ ትስስራችንን ለማጠናከር፣ እንዲሁም ቀጣይነት ያለው ጠንካራ ሀገረ መንግስትና ብሔረ መንግስት ለመገንባት እንቅፋት የሆኑ የተሳሳቱ ትርክቶችን መለየት እና ማስተካከያ ሊሆኑ የሚችሉ አማራጭ ሀሳቦችን በማቅረብ ወደ ተግባር መቀየር የሚያስችሉ ስልቶችን ይቀይሳል።

16. የአመራርና አባላትን አቅም መገንባት የሚያስችሉ ልሳናት እና የንድፈ ሃሳብ ጽሁፍ በተመረጡ ርዕሶች ላይ ጊዜያቸውን ጠብቀው በጥራት እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ የብልፅግና ቤተሰብና ህብረት ውጤታማ ውይይት እንዲደረግባቸው የድጋፍና ክትትል ሥራ መሰራቱን ያረጋግጣል፣

17. በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የፖለቲካ ስራዎችን በመስራት አዳዲስ አባላትንና ደጋፊዎችን በማፍራት ጠንካራ የአደረጃጀት ስራዎች መሰራታቸውን ያረጋግጣል፣

18. በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ ለሚገኙ አባሎቻችንና ደጋፊዎቻችን የፓርቲው በፕሮግራም፣ ማኒፌስቶው፣ የፓርቲው ልሳን፣ ከፓርቲዉ የበላይ አካል የሚተላለፍ የፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ዲፕሎማሲያዊ ውሳኔዎች እና ወቅታዊ ፅሑፎች ላይ ስልጠናዎችና ውይይቶች እንዲካሄድ ያቅዳል፣ያስፈጽማል፣የድጋፍና ክትትል ስራዎችን ይሰራል፣

19. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የመማር ማስተማሩ ሂደት ሰላማዊ እንዲሆን አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣

20. በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ የሚገኙ ምሁራንና የዩኒቨርስቲው ማህበረሰብ ለዘላቂ የሀገረ መንግስት ግንባታ እና ለህብረ - ብሄራዊ አንድነት የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ ተሳትፏቸው እንዲጎለብት የሚያስችሉ ስራዎች መሰራታቸውን ያረጋግጣል፣

21. በፖለቲካ ስራዎቻችን የተመዘገቡ ድሎችና ስኬቶችን መለየትና መቀመር ምርጥ ተሞክሮ እንዲሰፋ ያደርጋል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣

22. የብልፅግና ሴቶችና ወጣቶች ክንፎች ከፖለቲካ ስራዎች አኳያ ለክንፎች አኳያም ድጋፍ ያደርጋል፤በትብብር በጋራ ይሰራል፣
23. ቤተ-መፅሃፍት ያደራጃል፣ የአጠቃቀም ደንብ ያወጣል፣ ሂደቱን ይከታተላል፣
24. የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለፓርቲ ዋና ፅ/ቤት ኃላፊ ያቀርባል፤
25. ከጽ/ቤት ኃላፊ የሚሰጡ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

## ለ) የአደረጃጀት ዘርፍ

1) ተጠሪነቱ ለፓርቲው ዋና ጽ/ቤት ኃላፊ ይሆናል።
2) ዘርፉን በበላይነትና በሃላፊነት ይመራል
3) ከፓርቲ እቅድ በመነሳት የዘርፉን ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ሲጸድቅ ይፈፅማል፣ያስፈፅማል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ይደጋፋል፣ ይገመግማል፣
4) የዘርፉ ሥራዎች በአግባቡ እንዲከናወኑ ለሥራ ክፍሎች አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤ ያስተባብራል፤ ይከታተላል፤ በዘርፉ ስሩ ያሉትን ምክትል ዘርፍ ኃላፊና ዳይሬክቶሬቶች ይከታተላል፣ ይደግፋል፣ የሥራ አፈፃፀም ይገመግማል፣ ግብረ-መልስ ይሰጣል፣ ይመዝናል፣
5) የፓርቲ ደጋፊ አባላት በእቅድ እንዲመለመሉ፣ እንዲደራጁና በመደበኛነት የተግባቦት ውይይት እንዲደርጉና አቅም እንዲገነቡ ያስደርጋል፡
6) የፓርቲ አባላት ምልመላ ሥራዎች በፓርቲው የአሰራር ሥርዓቶች በጥብቅ ዲሰፕሊን ጠብቀው በጥራት መመልመላቸውን ያረጋግጣል፣ አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣ የአሰራር ጥሰት ሲያጋጥም የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤
7) የፓርቲ እጩ እና ሙሉ አባል በየደረጃው በብልፅግና ህብረትና በብልፅግና ቤተሰብ ተደራጅተው ተልዕኳቸውን አውቀው ለፓርቲው አቅም መሆናቸውን ያረጋግጣል፤
8) የፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ፣ መመሪያዎችና አሰራሮች በሁሉም አባላት፣ አመራርና አካላት በአግባቡ ታውቀው እንዲተገበሩ ያደርጋል፣ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣ የአሰራር ጥሰቶች ሲያጋጥሙ በፓርቲው የአባላትና አመራር ዲሲፕሊን መመሪያ መሰረት ተገቢው የእርምት እርምጃ እየተወሰደባቸው መሆኑን ያረጋግጣል፤
9) በየደረጃው የሚገኙ የፓርቲው አመራሮች፣ አባላትና አደረጃጀቶች በምዘና ማስፈፀሚያ መመሪያው መሰረት መመዘናቸውን ያረጋግጣል፤
10) በየደረጃው የሚገኙ የብልፅግና ቤተሰብ፣ የብልፅግና ህብረትና ንዑሳን ኮሚቴዎችን እንዲሁም የፓርቲ ደጋፊ ግለሰቦችና አባላት አደረጃጀቶች ጠንክረው የተሰጣቸውን ተልዕኮ በአግባቡ መወጣታቸውን ያረጋግጣል፤

11) በፓርቲው የውስጥ በየደረጃው የሚካሄዱ ምርጫዎች አሰራር ጠብቀው መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፣

12) የውስጠ-ፓርቲ ዴሞክራሲ እንዲጎለብት በየደረጃው የሚደረጉ ውይይቶች፣ ግምገማዎችና ክርክሮች የአባላት ተሳትፎ መረጋገጡን ይከታተላል፣ የአባላትን ነጻ ተሳትፎ የሚገድቡ ድርጊቶችን ተከስተው ሲገኙ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፣

13) በየደረጃው ያሉ የፓርቲው መዋቅሮች ግንባር ቀደም፣ ተኪና ኮር አመራር በአሰራር መመሪያው መሠረት መመልመላቸውንና በአመራር ቋት መያዛቸው ያረጋግጣል፤

14) አባላትና አመራሮች ለተለያዩ ሃላፊነቶች የሚደረጉ ምልመላዎች፣ ምደባዎች እና ሹመቶች እንዲሁም የስራ ስምሪቶች በፓርቲው የአሰራር መመሪያ መሰረት እንዲከናወኑ ያደርጋል፣

15) ሌብነትና ብልሹ አሰራሮች በየደረጃው በሚገኙ የፓርቲ አደረጃጀቶች፣ አካላትና አባላት ውስጥ ተቋማዊ በሆነ መልኩ የእቅድና የሪፖርት አካል ሆኖ ትግል እንዲደረግ ያደርጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ ጥፋቶች ሲፈጸሙ የእርምት እርምጃዎች እንዲወሰድ ያደርጋል፣

16) በሁሉም የአደረጃጀት ደረጃዎች /የብልፅግና ቤተሰብ፤ የብልፅግና ህብረት/ በተግባር ግንባር ቀደምና አርአያ የሆኑ አባላት እንዲመሩ የማድረግ ስራ ተሟልቶ መተግበሩን ያረጋግጣል፣

17) ለሀገራዊ የጠቅላላ፣ የአከባቢ፣ የማሟያና የድጋሚ ምርጫዎች ፓርቲውን ወክለው የሚወዳደሩ እጩዎችን በጥራት መለየት፣ ማስተቸት፣ አፈጻጸሙን መከታተልና የማዘጋጀት እንዲሁም ፓርቲውን ወክለው ምርጫውን የሚታዘቡ አባላትን መስፈርት ያዘጋጃል፣ በመስፈረት በመመልመል ለሚመለከተው አካል ዝርዝር መላክ፣

18) ለአቅም ግንባታ ስልጠናዎች፣ ለኮንፈረንሶች፣ ለጉባኤ እንዲሁም ለልዩ ልዩ ኩነቶች ተግባራት የሚመለመሉ አባላትና አመራሮች ስብጥሩን በጠበቀ መልኩ ግልጽ መስፈርት በማዘጋጀት እንዲመለመሉ ያደርጋል፤

19) የአመራርና የአባላት የፖለቲካ አቅም ግንባታ ሥልጠና ፕሮግራም ሲኖር የሠልጣኝ፣ የአሰልጣኝና የቡድን አወያይ ልየታ እንዲከናወን ያደርጋል፤ እንዲሁም ሰልጣኝ በቡድን እንዲደራጅ ያደርጋል፤ ለቡድን አወያይ ስምሪት ይሰጣል፤

20) የፓርቲ አባላትና አመራር መረጃዎችና ማህደሮች በቴክኖሎጂ በታገዘ መልኩ እንዲያዙ ያደርጋል፣ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣ ይህም የሚመራበት አሰራርና መመሪያ እንዲኖር ያደርጋል፤

21) የብልፅግና ፓርቲ አባላት፣ አመራር፣ አደረጃጀቶችና የተለያዩ የዘርፉን ሰነዶች ለመያዝ የሚያስችል ሶፍትዌር እንዲለማ ያስደርጋል፡

22) የአባላት መታወቂያ አዘገጃጀትና አሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣ ይከታተላል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፣

23) በየደረጃው በሚገኙ የፓርቲ መዋቅሮች ከአመራርና አባላት የሚቀርቡ ቅሬታዎች በአሰራር መመሪያ መሰረት ምላሽ ማግኘታቸውን ያረጋግጣል።

24) የፓርቲውን አሰራርና ደንብን የሚጥሱ አባላት እና የአመራር አካላት በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ተገቢው የእርምት እርምጃ እየተወሰደባቸው መሆኑን ያረጋግጣል፤ የእርምት እርምጃዎችን ይወስዳል፤

25) በሥራ ላይ የዋሉ የፓርቲ አሰራሮችና መመሪያዎች ለአባላትና አመራር ማሰልጠን እና ከየወቅቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር በመፈተሽ የማሻሻያ ሀሳብ ማደራጀት፣ ለሚመለከተው አካል ማቅረብ፤ እንዲሁም አዳዲስ አሰራሮችና አቅጣጫዎች በየጊዜው ተቀይሰው ተግባር ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤

26) የብልፅግና ሴቶችና ወጣቶች ክንፎች ከአደረጃጀት አኳያም ድጋፍ ያደርጋል፤በትብብር በጋራ ይሰራል፣

27) ከዘርፉ ሥራዎች ጋር በተያያዘ ምርጥ ተሞክሮ በመለየት እና ተሞክሮውን በመቀመር ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

28) የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለፓርቲ ዋና ፅ/ቤት ኃላፊ ያቀርባል፤

29) ከጽ/ቤት ኃላፊ የሚሰጡ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

**ሐ) የዴሞክራሲ ባህል ግንባታ ዘርፍ**

1. ተጠሪነቱ ለፓርቲው ዋና ጽ/ቤት ኃላፊ ይሆናል፣
2. ዘርፉን በበላይነትና በሃላፊነት ይመራል፣
3. ከብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽ/ቤት እቅድ በመነሳት የዘርፉን ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ሲጸድቅ ይፈፅማል፣ ያስፈፅማል፣ አፈፃፀሙን ይገመግማል፣
4. የዘርፉ ሥራዎች በአግባቡ እንዲከናወኑ ለሥራ ክፍሎች አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤ ያስተባብራል፤ ይከታተላል፤ በዘርፉ ስሩ ያሉትን ምክትል ዘርፍ ኃላፊና ዳይሬክቶሬቶች ይከታተላል፣ ይደግፋል፣ የሥራ አፈፃፀም ይገመግማል፣ ግብረ-መልስ ይሰጣል፣ ይመዝናል፣
5. በአገሪቱ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች የፓርቲዎችን ይደግፋል ፣ በፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ፓርቲውን ወክሎ ይሳተፋል፣ በመወያየት እና በመመካከር

በዴሞክራሲያዊ ስርዓትና ባህል ግንባታ ሂደት ውስጥ ገንቢ ሚና እንዲጫወቱ አብሮ ይሰራል፣

6. በአገሪቱ የሚንቀሳቀሱ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ለኢኮኖሚ ዕድገትና ብልፅግና፣ ለማህበራዊ ልማትና ፍትህ፣ ለሲቪልና ዲሞክራሲ ባህል ግንባታ፣ ለሠላም እና ለዜጋ ዲፕሎማሲ ሚናቸው እንዲያድግ በትብብር ይሰራል፣
7. በሲቪክ፣ የሙያና የብዙሃን ማህበራት፣ የግል ዘርፍ ማህበራት፣ ፌዴሬሽኖች፣ ፎረሞች፣ ሌሎች የምሁራንና የባለሃብት አደረጃጀቶች እንዲሁም የህብረተሰብ ተቋማትና አደረጃጀቶች ለሲቪልና ለዲሞክራሲ ባህል ግንባታ ሚናቸዉን እንዲወጡ በትብብር ይሰራል፣ ይደግፋል፣
8. የፓርቲውን የብልፅግና ሴቶችና ወጣቶች ክንፎች በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ የተሰጣቸውን ተግባራትና ኃላፊነቶች እንዲወጡ ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፣
9. ፓርቲው ከኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ጋር ያለውን ህጋዊና ተቋማዊ የስራ ግንኙነት ፓርቲውን በመወከል ያስተባብራል፤
10. የምርጫ ሂደት ስራዎችን ፓርቲዉን በመወከል ያስተባብራ፣ ይከታተላል ይደግፋል፣
11. የዲሞክራሲ ሥርዓትን በተቋምና ባህል የመገንባት ስራዎች ላይ ፓርቲዉን በመወከል የዲሞክራሲ ተቋማትን ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል
12. ከዘርፉ ሥራዎች ጋር በተያያዘ ከባለድርሻ አካላት ጋር የሚሠሩ የፖለቲካ፣ የአደረጃጀት እና የተግባቦት ስራ ላይ ከሌሎች ዘርፎች ጋር በመቀናጀት ይሰራል፣
13. የዘርፉን መረጃዎችን ያደራጃል፣ ያጠናቅራል፣ ሪፖርት ያደርጋል፣
14. ከዘርፉ ሥራዎች ጋር በተያያዘ ምርጥ ተሞክሮ በመለየት እና ተሞክሮውን በመቀመር ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤
15. የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለፓርቲ ዋና ፅ/ቤት ኃላፊ ያቀርባል፤
16. ከፓርቲ ዋና ፅ/ቤት ኃላፊ የሚሰጡ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፣

**መ) የህዝብና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ዘርፍ**

1. ተጠሪነቱ ለፓርቲው ዋና ጽ/ቤት ኃላፊ ይሆናል።
2. ዘርፉን በበላይነትና በሃላፊነት ይመራል፣
3. ከብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽ/ቤት እቅድ በመነሳት የዘርፉን ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ሲጸድቅ ይፈፅማል፣ ያስፈፅማል፣ አፈፃፀሙን ይገመግማል፣ ፣

4. የዘርፉ ሥራዎች በአግባቡ እንዲከናወኑ ለሥራ ክፍሎች አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤ ያስተባብራል፤ ይከታተላል፤ በዘርፉ ስሩ ያሉትን ምክትል ዘርፍ ኃላፊና ዳይሬክቶሬቶች ይከታተላል፣ ይደግፋል፣ የሥራ አፈፃፀም ይገመግማል፣ ግብረ-መልስ ይሰጣል፣ ይመዝናል፣
5. የፓርቲው ፕሮግራም፣ ማኒፌስቶ፣ እሳቤዎች፣ ዓላማዎችና እሴቶች በህዝቡ በአግባቡ እንዲታወቁ በመደበኛና ማህበራዊ ሚዲያ በመጠቀም የብሔራዊነት፣ የወንድማማችነት እና እህትማማችነት እና ህብረ-ብሔራዊ አንድነት ትርክት የበላይነት እንዲሰርጽ ይሰራል፣
6. የፓርቲው ያስመዘገባቸው አገራዊና ክልላዊ ስኬቶች በህዝቡ ልብ ውስጥ እንዲሰርጽ ያደርጋል፣
7. የፓርቲውን መልካም ገጽታ ይገነባል፤ የፓርቲዉን መልካም ስም የሚያጠለሹ ጉዳዮችን በመከታተል ይመክታል፣
8. የፓርቲው የፖለቲካና የአደረጃጀት ሥራዎችና ውሳኔዎች በተለያዩ የብዙሃን መገናኛ ዘዴዎች ሽፋን እንዲያገኙ ያደርጋል፤ በቀጣይነት የማስተዋወቅ ስራ ይሰራል፣
9. ፓርቲው በሚያዘጋጃቸው ስልጠናዎች፣ ኮንፈረንሶችና መሰል ውይይቶች ለሚዲያዎች መግለጫዎችና ፕሬስ ኮንፈረንሶችን ያዘጋጃል ይሰጣል፣
10. የአመራሩን የፓርቲ የውስጥ ኮሚዩኒኬሽንን ማጠናከር የሚያስችል ስልት ይነድፋል፤ ተግባራዊም ያደርጋል፤
11. ከተለያዩ የሚዲያ አካላት ጋር በመተባበር ስለፓርቲው ወቅታዊ መረጃዎችን ይሰጣል፣
12. የሚዲያ ዳሰሳ እና የሕዝብ አስተያየት ዳሰሳ ያደርጋል፣ ግኝቶችን ያቀርባል፣ ሲወሰን ጥቅም ላይ ያውላል፣
13. የፓርቲውን ዓለም አቀፍ እና የፓርቲ ለፓርቲ ግንኙነት የማጠናከር ሥራዎችን በበላይነት ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ይከታተላል፣
14. ከዘርፉ ሥራዎች ጋር በተያያዘ ምርጥ ተሞክሮ በመለየት እና ተሞክሮውን በመቀመር ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤
15. ከተለያዩ የሚዲያ አካላት ጋር በመተባበር ስለፓርቲ ወቅታዊ መረጃዎችን ይሰጣል፣
16. የህዝቡን ሁለንተናዊ የለውጥ እንቅስቃሴ ይዘግባል፣ የህዝቡን ወቅታዊ ፍላጎት በዳሰሳ መለየትና በተለዩት ጉዳዮች ላይ የፓርቲው አቋም በተለያዩ ዘዴዎች ያሰራጫል፤
17. የፓርቲውን አቋሞች፣ ፖሊሲዎችና ያስመዘገባቸውን ለውጦች በህትመት፣ በኦዲዮ-ቪዥዋል አዘጋጅቶ ያሰራጫል፣
18. የፓርቲውን ፅ/ቤት ዌብሳይት፤ የማህበራዊ ገጾችን በይዘት ማጠናከርና የፓርቲው የመረጃ ማሰራጫ እንዲሆኑ ያደርጋል፣

19. የአገር ውስጥ እና የውጪ ሚዲያዎችን በንቃትና በብቃት ቀጣይነት ባለው መልኩ በመከታተል መረጃዎቹን በማደራጀትና በመተንተን ለቀጣይ ስራ በግብአትነት ይጠቀማል፤ ለሚመለከታቸው አደረጃጀቶችም መረጃዎችን ያደርሳል፤
20. የተለያዩ የፓርቲው ኩነቶች (ጉባኤ፣ ኮንፈረንስ፣ ኤግዚቢሽን እና የተለያዩ መድረኮችን) እንዲዘጋጁ ያስተባብራል፤ ለገጽታ ግንባታም ያውላል፤
21. ለተለያዩ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር የሚዲያ ተቋማት የሚመጡ የመረጃ ጥያቄዎችና የፓርቲውን ፍላጎት መሰረት አድርጎ ምላሽ ይሰጣል፣
22. ወቅታዊ ክስተቶችን በመከታተል በእቅድ የተመራ የህዝብ ግንኙነት ስራዎችን ይሰራል፤
23. የብልፅግና ፓርቲ በውጭ አገራት የሚያደርገውን የልምድ ልውውጥና የተለያዩ ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ መድረኮች ተሳትፎ ይመራል፤ ያስተባብራል፤
24. ከውጭ ፓርቲዎች ጋር የተጀመረውን ግንኙነት ያጠናክራል፤ በጥናት ላይ ተመስርቶ አዳዲስ ግንኙነቶችን ይፈጥራል፤
25. የፓርቲውን አጠቃላይ ገጽታ በውጭ ፓርቲዎች፣ በሃገራችን በሚገኙ ኤምባሲዎችና በተለያዩ ዓለም አቀፋዊና አህጉራዊ ተቋማት የሚደረገውን የገጽታ ግንባታ ይሰራል፣ ያስተባብራል፤
26. የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለፓርቲ ዋና ፅ/ቤት ኃላፊ ያቀርባል፤
27. ከፓርቲ ዋና ፅ/ቤት ኃላፊ የሚሰጡ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፣

**ሠ) የጥናትና ምርምር ዘርፍ**

1. ተጠሪነቱ ለፓርቲው ዋና ጽ/ቤት ኃላፊ ይሆናል።
2. ዘርፉን በበላይነትና በሃላፊነት ይመራል፣
3. ከብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽ/ቤት እቅድ በመነሳት የዘርፉን ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ሲጸድቅ ይፈፅማል፣ ያስፈፅማል፤ አፈፃፀሙን ይገመግማል፣ ፣
4. በዘርፉ ሥራዎች በአግባቡ እንዲከናወኑ ለሥራ ክፍሎች አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤ ያስተባብራል፤ ይከታተላል፤ በዘርፉ ስሩ ያሉትን ምክትል ዘርፍ ኃላፊና ዳይሬክቶሬቶች ይከታተላል፣ ይደግፋል፣ የሥራ አፈፃፀም ይገመግማል፣ ግብረ-መልስ ይሰጣል፣ ይመዝናል፣
5. የፓርቲውን ዋና ጽ/ቤት የአሰራር ሥርዓት ዘመናዊና ቀልጣፋ ሊያደርጉ የሚችሉ ልዩ ልዩ ጥናቶችን በማጥናት እና የተለያዩ ተሞክሮዎችን በመቀመር ያቀርባል፤ ሲወሰን እንዲተገበር ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣

6. የፓርቲውን የፖሊሲና ስትራቴጂ ሀሳቦችን አጥንቶ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም የተጠበቀውን ውጤት ማምጣታቸውን ይከታተላል፣
7. የፓርቲ ውስጣዊ ጤንነትና ውጤታማነት እና የፓርቲ አባላትና አመራር አስተያየት የዳሰሳ ጥናት በማድረግ ያቀርባል፣
8. በፓርቲ የሚሰጡ ስልጠናዎች ያመጡት ተፅዕኖና ውጤት በሚመለከት የዳሰሳ ጥናት በማድረግ ያቀርባል፣
9. በየደረጃው የፓርቲ መዋቅሮች ጠንካራ እና የተጽዕኖ አድማሳቸው የሚያድግበትና የፓርቲውን ቅቡልነት የሚጠናከርበት ስልቶችን አጥንቶ ያቀርባል፣ ውሳኔ ሲያገኝም እንዲተገበር ያደርጋል፣
10. የፓርቲውን ስታቲስቲካዊ መረጃዎች ይሰበስባል፣ ያደራጃል፣ ሲወሰን አሳትሞ ያሰራጫል፣
11. የዘርፉን መረጃዎችን ያደራጃል፣ ያጠናቅራል፣ ሪፖርት ያደርጋል፣
12. ከዘርፉ ሥራዎች ጋር በተያያዘ ምርጥ ተሞክሮ በመለየት እና ተሞክሮውን በመቀመር ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤
13. የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለፓርቲ ዋና ፅ/ቤት ኃላፊ ያቀርባል፤
14. በፓርቲው ፍልስፍና፤ ፖለቲካ፤ ኢኮኖሚ፤ ማህበራዊ እና ዴሞክራሲያዊ ግንባታ ጉዳዮች ላይ ቀጣይነት ያለው ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፤
15. በቁልፍ እና ተለዋዋጭ የአገራችን ፖለቲካ-ኢኮኖሚ ጉዳዮች ዙሪያ ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፤
16. የምሁራን አሰላሳይ አደረጃጀቶች እንዲፈጠሩ ድጋፍ ያደርጋል፣ ከአደረጃጀቶቹ ጋር በመተባበር በተመረጡ አገራዊና ዓለም ዓቀፋዊ ጉዳዮች ላይ ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፣ ውጤቱንም ለቀጣይ ስራ ያዘጋጃል፤
17. ከተለያዩ አገር በቀል እና ዓለም አቀፍ የጥናትና ምርምር ተቋማት ጋር የመግባቢያ ሰነድ ከጽ/ቤት ሃላፊ ጋር በመነጋገር ሊፈርም ይችላል፣
18. የጥናትና ምርምር ውጤቶችን መለየት፤ ማሰባሰብና ለጥናትና ምርምር ግብዓት እንዲሆኑ ያዘጋጃል፤
19. የፓርቲው ዋና ጽ/ቤት ስራ አመራር ኮሚቴና ዘርፍ አመራሮች በሚለዩዋቸው አገራዊ ርዕሶች ላይ ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፤
20. ፓርቲው ያለፈባቸውንና የሚያልፍባቸውን የትግል ምዕራፎች በጥናትና ምርምር በመቀመር አዲሱ ትውልድ እንዲያውቃቸውና ለሚቀጥለው ትውልድ የሚተላለፍ የተደራጀ ሰነዶች ያዘጋጃል፤

21. የፖለቲካና አቅም ግንባታ ሰነዶች ከፓርቲው ከህብረተሰብ ክፍል የግንዛቤ ደረጃ ጋር የተጣጣመ መሆኑን ከሚመለከተው ዘርፎች ጋር ያረጋግጣል፣
22. የፓርቲውን እሳቤ ስርፀት ላይ የሚታዩ ክፍተቶችን በመለየት ለቀጣይ ጥናትና ምርምር ግብዓት እንዲሆን ይጠቀማል፣
23. ለፓርቲው ስራ ጠቃሚ ናቸው ተብሎ የታመኑባቸውን አለም አቀፍ ልምዶችን አጥንቶ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣
24. የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለፓርቲ ዋና ፅ/ቤት ኃላፊ ያቀርባል፤
25. ከፓርቲ ዋና ፅ/ቤት ኃላፊ የሚሰጡ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፣

## ረ) የስትራቴጂክ ስራ አመራርና ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍ

1. ተጠሪነቱ ለፓርቲው ዋና ጽ/ቤት ኃላፊ ይሆናል።
2. ዘርፉን በበላይነትና በሃላፊነት ይመራል፣
3. የብልፅግና ፓርቲ ፅ/ቤቱን ስትራቴጂክ ዕቅድ በማዘጋጀትና በማጸደቅ በዕቅዱ መሰረት የጽ/ቤቱ ዘርፎች እና ክፍሎች እንዲሁም የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ስትራቴጂውን በአግባቡ ማውረዳቸውንና ዓመታዊ ዕቅዳቸውን በሚገባ ማዘጋጀታቸውን ይከታተላል፣ ድጋፍም ይሰጣል፤
4. የዘርፉ ሥራዎች በአግባቡ እንዲከናወኑ ለሥራ ክፍሎች አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤ ያስተባብራል፤ ይከታተላል፤ በዘርፉ ስሩ ያሉትን ዳይሬክቶሬቶች ይከታተላል፣ ይደግፋል፣ የሥራ አፈፃፀም ይገመግማል፣ ግብረ-መልስ ይሰጣል፣ ይመዝናል፣
5. በየወቅቱ የሚዘጋጁ የሥራ ክፍሎች እቅድና አፈጻጸም ከስትራቴጂክ ዕቅዱ ጋር ተናቦ መዘጋጀቱን እና መከናወኑን ያረጋግጣል፣
6. በፓርቲውን ጽ/ቤቱ ዓመታዊ ዕቅድ ላይ የጽ/ቤቱን ሰራተኛ ግንዛቤ ወስዶ መፈፀም እንዲችል በየደረጃው የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን እንዲመቻች በማድረግ፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤
7. በፅ/ቤቱ የሚገኙ የሥራ ክፍሎች ዕቅድ መናበቡን ያረጋግጣል፣ የሪፖርት አቀራረብ፣ የግምገማና ግብረ-መልስ አሰጣጥ የአሰራር ሥርዓት ተከትሎ እንዲዘረጋ ያደርጋል፣
8. ከጽ/ቤቱ የሥራ ክፍሎች የሚቀርቡ ዕቅዶችንና፤ የተጠቃለለ ሪፖርት መዘጋጀቱን ያረጋግጣል

9. የተለያዩ የሥራ ክፍሎችን በማወያየት ችግሮችን ይለያል እንደክብደታቸው ቅድም ተከተል በማደራጀት በአጭር፣ በመካከለኛና በረጅም ጊዜ የሚፈቱበትን መፍትሔ ሀሳብ ያቀርባል።
10. የዘርፎችና የሥራ ክፍሎች በሚቀርቡ ሪፖርት አጠቃላይ ይዘትና ዕቅድ አፈፃፀም ላይ ግብረ-መልስ ይሰጣል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፣
11. የጽ/ቤቱን የዕቅድና የፕሮግራሞች በጀት ዝግጅትና አጠቃቀም በመከታተልና በመገምገም ለፕሮግራም በጀት ባለቤቶች በየጊዜው ግብረመልስ በመስጠት ወደሚመለከተው ሪፖርት ያደርጋል፣
12. ከተለያዩ የሥራ ክፍሎች የሚቀርቡ ፕሮጀክቶች ሥራዎች ጥራትና ወቅታቸውን ጠብቀው መተግበራቸውን ይከታተላል፣
13. የዋናው ጽ/ቤትና የቅርንጫፍ ፅ/ቤቶች የሚገኙ የሥራ ክፍሎችን ከስራ ክፍሉ ሥራዎች ጋር በተያያዘ የግንኙነት ሥርዓት ይዘረጋል፤ ወቅታዊ ሪፖርትና አጋዥ መረጃዎች እንዲቀርቡ ያደርጋል፤
14. የጽ/ቤቱን የሥራ ዘርፎች ዕቅድ አፈፃፀም የመስክ ሱፐርቪዥን በየስድስት ወሩ በማድረግ ከዘርፎች ጋር በማቀናጀት ወቅቱን ጠብቀው እንዲከናወኑ ያደርጋል።
15. የዋና ጽ/ቤት ዕቅዶች በተያዘላቸው ጊዜ፣ መጠን፣ ጥራትና ወጪ መሰረት መከናወናቸውን በመከታተልና በአግባቡ መፈፀማቸውን በማረጋገጥ የድጋፍ ተግባራትን ያከናወናቸውን
16. የጽ/ቤቱ ዘርፎችን በተቀመጡ ግቦች መሠረት መፈጸማቸውን ይከታተላል፤ይገመግማል፤ ይመዝናል፤ ግብረ-መልስ ይሰጣል፣ ክፍተቶች የሚሻሻልበትን የመፍትሄ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣
17. በዋና ጽ/ቤት እና በቅ/ጽ/ቤቶች የአንድ ዕቅድ የአንድ ሪፖርት ስርዓት እንዲዘረጋ በማድረግ አፈጻጸም ይከታተላል፣
18. የበሩብ ዓመቱ የዋናው ጽ/ቤት እና ቅ/ጽ/ቤቶች የእቅድ አፈጻጸማችን ግምገማ መድረኮች ያመቻቻል
19. የዋናው ጽ/ቤት እና ቅ/ጽ/ቤቶች የአመራሮችና ሠራተኞች ምዘና ስርዓት (70%) የምዘና መስፈርቶችን አዘጋጅቶ ተግባራዊ እንዲደረጉ ይሠራል።
20. የፓርቲ መዋቅር አመራሮች እና ሠራተኞች የእውቅናና ሽልማት ስርዓት አሰራር መዘርጋት እና በየዓመቱ የእውቅና ሽልማት መርሃ ግብሮችን ያዘጋጃል።

21. የጽ/ቤቱን የኔትወርክ እና ዲጂታላይዜሽን ስራዎች ያቅዳል፤ያቀናጃል፤ያስተዳድራል ፤ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል ፤ አዲስ የኔትወርክ ዝርጋታ ስራን ለማከናወን የሚያስችለውን የወጪ ግምትና የሰው ኃይል ዕቅድ በማዘጋጀት መተግበር ፤አፈጻጸሙንም መከታተል ፤
22. የጽ/ቤቱን የዌብ ሳይት አገልግሎት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን፣ ይከታተላል፤ ይገመግማል፣
23. በማዕከል ደረጃ የተደረጀና የተቀናጀ የሁሉንም የሥራ ክፍሎች የመረጃ አያያዝ ስርዓት ስራ ላይ ማዋሉን ይከታተላል ፣ይገመግማል
24. የኔትወርክ ሲስተም በመጠበቅና የሚያጋጥሙ ችግሮችን በወቅቱ እንዲፈቱ ድጋፍ ያደርጋል
25. በጽ/ቤቱ የተደራጁ የሥራ ክፍሎች እና በፅ/ቤቱ ደረጃ በተቀመጡ ግቦች መሠረት መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፤ ይገመግማል፣ ግብረ-መልስ ይሰጣል ክፍተቶች የሚሻሻሉበትን የመፍትሄ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣
26. የአይሲቲ መሰረተ ልማት እንዲሟሉ ያደርጋል፣
27. የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለፓርቲ ዋና ፅ/ቤት ኃላፊ ያቀርባል፤
28. ከጽ/ቤት ኃላፊ የሚሰጡ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፤

### ሰ) የሀብት አስተዳደር ዘርፍ

1. ተጠሪነቱ ለፓርቲው ዋና ጽ/ቤት ኃላፊ ይሆናል
2. ዘርፉን በበላይነትና በሃላፊነት ይመራል፣
3. ከብልፅግና ፓርቲ እቅድ በመነሳት የዘርፉን ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ሲጸድቅ ይፈፅማል፣ ያስፈፅማል፤ አፈፃፀሙን ይገመግማል፣ ፣
4. በዘርፉ ሥራዎች በአግባቡ እንዲከናወኑ ለሥራ ክፍሎች አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤ ያስተባብራል፤ ይከታተላል፤ በዘርፉ ስር ያሉትን ዳይሬክቶሬቶች ይከታተላል፣ ይደግፋል፣ የሥራ አፈፃፀም ይገመግማል፣ ግብረ-መልስ ይሰጣል፣ ይመዝናል፣
5. የፓርቲው ፋይናንስ አሠራር ሥርዓት መሠረት በአግባቡ ሥራ ላይ ያውላል፣ ይከታተላል፣ **የእርምት እርምጃም ይወስዳል፣**
6. የፓርቲው ንብረቶች በአግባቡ ተመዝግበው እንዲታወቁ፣ እንክብካቤ እንዲደረግላቸውና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣
7. የፓርቲ አባልነት መዋጮ እና ከልዩ ልዩ ድጋፎች የሚገኘው ገቢ በፓርቲ ህጋዊ ደረሰኝ ተሟጦ ተሰብስቦ ገቢ መሆኑን ያረጋግጣል፣

8. የፓርቲ ፋይናንስና ንብረቶች በአሰራር በተቀመጠው መሠረት በውስጥና በውጭ ኦዲተሮች ኦዲት እንዲሆኑ ያደርጋል፣ የኦዲት ግኝቶችን የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፣ ይከታተላል፣ **ክዋኔ ኦዲትም ያስደርጋል፣**
9. የፓርቲ ዋና ፅ/ቤት እና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚገኙትን የሰው ሀብት አስተዳደር ሥራዎች የአሰራር መመሪያዎችን ተከትሎ ወጥነት ባለው መንገድ ስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፣
10. የፓርቲ ዋና ፅ/ቤት እና የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በጀት ለታቀደለት ዓላማ መዋሉን ያረጋግጣል፣ የበጀት አጠቃቀም ሪፖርት አቀናጅቶ ያቀርባል፣ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የገቢና የወጪ ሪፖርታቸዉን በተቀመጠ የጊዜ ገደብ እንዲያቀርቡ ይከታተላል፣
11. የፓርቲ የፋይናንስ ሰነዶች በአግባቡ እንዲጠበቁ ያደርጋል፣ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ገቢ ከተሰበሰበ በኋላ በየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ተሰብስበዉ መቀመጣቸዉን ይከታተላል፣
12. የፓርቲ ዋና ፅ/ቤቱን የጠቅላላ አገልግሎት ሥራዎችና የስራ ቦታ ምቹ መሆኑን ያረጋግጣል፣
13. የፓርቲ ዋና ፅ/ቤት አመራርና ሰራተኞች መካከል መከባበር፣ መተሳሰብና የወንድማማችነት/የእህትማማችነት እና ሰዋዊ እሴቶች እንዲያዳብሩ የማትጊያ ስልቶችን ይቀይሳል፣ ሲወሰን ይተገብራል፣
14. የዘርፉን መረጃዎችን ያደራጃል፣ ያጠናቅራል፣ ሪፖርት ያደርጋል፣
15. ከዘርፉ ሥራዎች ጋር በተያያዘ ምርጥ ተሞክሮ በመለየት እና ተሞክሮውን በመቀመር ሲፀድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤
16. የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለፓርቲ ዋና ፅ/ቤት ኃላፊ ያቀርባል፤
17. ለፅ/ቤቱ የሚያስፈልጉ ክፍት የሥራ መደቦች ላይ ብቃት ያላቸው **ወጣት** ባለሙያዎችን በፅ/ቤቱ በተቀመጠ ህግ መሰረት ብዝሃነትን ባማከለ አግባብ በቅጥር፤ በዕድገትና በዝውውር እንዲሟሉ ያደርጋል፣ የቡድን መሪዎች ቅጥርና ምደባ ያፀድቃል፣ የሠራተኞች ቅጥር፤ ዕድገት፤ ዝውውርና የጡረታ ጊዜ ማራዘሚያ የውሳኔ ሀሳብ መርምሮ ያፀድቃል።
18. የፅ/ቤቱ አመራሮችና ሰራተኞች የአመለካከት፤ የዕውቀትና የክህሎት ብቃት ክፍተቶችን በመለየት ስልጠናዎች እንዲያገኙ ያደርጋል፣ የስልጠናውን ውጤታማነት ይገመግማል፣
19. የሰራተኞች መብቶችና ጥቅማ ጥቅሞች መከበራቸውንና ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች ለሰራተኞች መሟላታቸውን ያረጋግጣል፣

20. ከሰራተኞች የሚቀርቡ ቅሬታዎችን በወቅቱ እንዲፈቱ ያደርጋል፣ ይከታተላል፣ የቅሬታና የዲሲፕሊን ኮሚቴዎች የተሰጣቸውን ተልዕኮ በአግባቡ እንዲወጡ ይደግፋል፣ ይከታተላል፣ እንዲጠናከሩ ያደርጋል።
21. የፅ/ቤቱ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ከሙስናና ብልሹ አሰራር በፀዳ መልኩ በሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፣ የበጀት አጠቃቀም ሪፖርት፣ የሂሳብ ትንተና የባንክ ማስታረቅ ሥራዎችና የሂሳብ መግለጫዎች በየወቅቱ መዘጋጀታቸውን ያረጋግጣል፣
22. በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የሂሳብ መግለጫዎች ተዘጋጅተው ለኦዲት ምርመራ እንዲቀርቡ ያደርጋል።
23. ክፍያዎች አስፈላጊው መረጃዎች ተሟልተውላቸው መቅረባቸውና በጀት የተያዘላቸው መሆናቸው ተረጋግጦ ክፍያ በየወቅቱ መፈፀሙን ያረጋግጣል።
24. በውስጥ ኦዲትና በውጭ ኦዲተሮች የሚደረጉ የኦዲት ሥራዎች እንዲሳኩ ምቹ ሁኔታ እንዲመቻች ያደርጋል፣ የሚቀርቡ የኦዲት ግኝትና ጉድለት ሪፖርቶች ላይ ለዘርፉ ተጠሪ የሆኑ የሥራ ክፍሎች በወቅቱ የማስተካከያ መርሀ-ግብር አዘጋጅተው አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ መውሰዳቸውን ያረጋግጣል፣ ግብረ መልስ ይሰጣል፤ የክትትል ሪፖርት ያቀርባል።
25. በዋና ጽ/ቤትና በቅርንጫፎች የሚሰበሰቡ ገቢዎች በሙሉ በወቅቱ መሰብሰባቸውንና የባንክ ሂሳብ ገቢ መደረጋቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣ ይደግፋል፣ ይገመግማል።
26. የተንጠለጠሉ ውዝፍ ሂሳቦችን በመለየት፤ ሊሰበሰቡ የሚችሉትን ሂሳቦች በመሰብሰብ እንዲሁም ሊሰበሰቡ የማይችሉትን ከበቂ መረጃ ጋር እንዲሰረዙ የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል።
27. የፅ/ቤቱ የጠቅላላ አገልግሎት ሥራዎች፣ የተሽከርካሪዎች ስምሪትና አስተዳደር፣ የነዳጅና ቅባት አጠቃቀም የመንግስት ህግና ደንብን ተከትሎ መፈፀሙን ያረጋግጣል፣ ችግሮች ሲከሰቱ እንዲፈቱ ያደርጋል።
28. የተለያዩ አገልግሎቶች (utility) ባልተቆራረጠ ሁኔታ መሰጠታቸውን እንዲሁም የአገልግሎት ክፍያ በወቅቱ መፈፀሙን ይከታተላል፣
29. በግልፅ ጨረታ፣ በማዕቀፍ፣ በቀጥታና በፕሮፎርማ የሚገዙ የዕቃና የአገልግሎት ግዥዎች ህግን ተከትለው መፈፀማቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣
30. የግዥ ክፍያዎች ሰነዶች ተሟልተው መቅረባቸውን በማረጋገጥ በመመሪው መሰረት ክፍያ ያፀድቃል፤ እንዲፈፀምም ያደርጋል፣
31. የአገልግሎት አጠቃቀምና ክፍያዎች ህጎችን ተከትለው መፈፀማቸውን ይከታተላል፣ በሚታዩ ክፍተቶች ላይ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፣

32. በዋናው ጽ/ቤትና የቅርንጫፍ ፅ/ቤቶችን የሚገኙ የሥራ ክፍሎችን ከዳይሬክቶሬቱ ሥራዎች ጋር በተያያዘ የግንኙነት ሥርዓት ይዘረጋል፤ ሪፖርትና አጋዥ መረጃዎች እንዲቀርቡ ያደርጋል፤ እንደአስፈላጊነቱ የሚመለከታቸውን ኃላፊዎችና ባለሙያዎች መድረክ በማዘጋጀት ያወያያል፤ በውይይቱ ወቅት የተወሰኑ ውሳኔዎች መፈፀማቸውን ይከታተላል፤ ይደግፋል፤

33. ለፅ/ቤቱ ሥራዎች አስፈላጊ የሆኑ ቢሮዎች የማደራጀትና የቢሮ መገልገያ መሳሪያዎችን ስታንዳርድ ተዘጋጅቶ ሲወሰን እንዲሟላ ያደርጋል፣

34. ተቋማዊ የሰው ኃይል የአቅም ግንባታ ፕሮግራም በማዘጋጀት ተግባራዊ ያደርጋል፣ የክዋኔ አመራር ሥርዓት በማዘጋጀት ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣

35. የፋይናንስ ሥርዓትን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ ዘመናዊ ፋይናንስ ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፣

36. የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ለፓርቲ ዋና ፅ/ቤት ኃላፊ ያቀርባል፤

37. ከፓርቲ ዋና ፅ/ቤት ኃላፊ የሚሰጡ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል

3) **በዋና ጽ/ቤት ስር ለተደራጁ ዘርፎች የተሰጡ ተግባራትና ኃላፊነቶች በየደረጃው በሚገኙ የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ስር ለተደራጁ ዘርፎችም ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።**

4) **የዘርፎች አሰራር የሚከተለው ይሆናል፣**

   1) በየአስራ አምስት ቀን መደበኛ ስብሰባ ያደርጋሉ፣
   2) በየወሩ ከክልሎች ሪፖርት ይቀበላል
   3/ ዘርፎች በየደረጃው ከሚገኙ ተመሳሳይ ዘርፎች ጋር በየሶስት ወሩ የእቅድ አፈጻጸም ግምገማ የጋራ የውይይት መድረክ ያካሂዳሉ።
   4) በየደረጃው የሚገኙ ዘርፎች ተጠሪነታቸዉ ለየደረጃዉ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሃላፊ እና ከፍ ብሎ ለሚገኘዉ ተመሳሳይ ዘርፍ ይሆናል፣

## 12.የፌዴራል ተቋማት አስተባባሪ አደረጃጀት

1) በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 30 (2) በተደነገገው መሠረት የፌዴራል ተቋማት አደረጃጀት የሚመራና የሚያስተባብር ከሰባት እስከ ዘጠኝ አባላት የያዘ በፓርቲ ዋና ጽ/ቤት ኃላፊ የሚመደቡ አባላት ያሉት አስተባባሪ ኮሚቴ ይኖራል፣ የአስተባባሪ ኮሚቴ ሰብሳቢ የፓርቲ ዋና ጽ/ቤት አደረጃጀት ዘርፍ ኃላፊ ይሆናል።ከአስተባባሪ ኮሚቴ መካከል

3 ወይም 4 አባላት የፖለቲካ ንዑስ ኮሚቴ እና 3 ወይም 4 አባላት የአደረጃጀት ንዑስ ኮሚቴ ይኖራቸዋል።

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተደነገገው መሰረት አንድ ክላስተር ቢያንስ አምስት ወረዳዎችን አቅፎ የሚደራጅ ይሆናል።

3) ከፓርቲ ዋና ጽ/ቤት ለፌዴራል ተቋማት አደረጃጀት እና ለክላስተሮች አንዳንድ ቋሚ ሴክሬተሪያት የሚመደቡ ይሆናል፣

4) ለፌዴሬል ተቋም ወረዳ ከመደበኛ ስራቸው ጋር ደርበው የሚሰሩ አንዳንድ ሴክሬተሪያት እንዲደራጁ ይደረጋል።

## 13.የፌዴራል ተቋማት አስተባባሪ ኮሚቴ ተግባራትና ኃላፊነቶች

1. የፌዴራል ተቋማት የፖለቲካና የአደረጃጀት ሥራዎች በበላይነት ያስተባብራል፤
2. ከፓርቲ ዋና ጽ/ቤት የሚወርዱ ዕቅድን መነሻ በማድረግ አመታዊ እቅዱን ያዘጋጃል፣ ፈፃሚ አካላትን ለስራው ያዘጋጃል፤ ያሰማራል በስራው ሂደትም ተከታትሎ ይደግፋል።
3. የአባላትና የአመራር የስልጠና ስራ ያቅዳል፣ ያደራጃል ስልጠናውም እንዲካሄድ ያደርጋል።
4. የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ፣ መመሪያዎች፣ ውሳኔዎችና አቅጣጫዎችን ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ በአፈጻጸም የሚያጋጥሙ ችግሮችን ይለያል፣ መፍትሄ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣
5. የአባላትን መረጃዎች በአግባቡ ይይዛል፣
6. የፓርቲውን የፖለቲካ ጥራትና የስነ-ምግባር ውጤታማነት እንዲረጋገጥ አቅዶ ይሰራል፣ ይከታተላል፣
7. የውስጠ-ፓርቲ ዴሞክራሲ እንዲጎለብት በውይይቶች፣ በግምገማዎችና በክርክሮች ላይ የአባላት ተሳትፎ እንዲረጋገጥ ይሰራል፣ የአባላትን ነጻ ተሳትፎ የሚገድቡ ድርጊቶችን እንዳይኖሩ ያደርጋል፣
8. ሌብነትና ብልሹ አሰራሮች ተቋማዊ በሆነ መልኩ ትግል እንዲደረግ ያደርጋል የሚፈጸሙ ጥፋቶች የፓርቲ አሰራሮች ጠብቆ የእርምት እርምጃዎች ያስወስዳል ፣
9. ከፌዴራል ተቋማት ኮሚሽን የሚሰጡ የኢንስፔክሽን ግኝቶች ምክረ-ሐሳቦችና ውሳኔዎችን በመውሰድ ተገቢነቱን መርምሮ ተግባራዊ ያደርጋል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፣ የአፈጻጸሙን ያሳውቃል፣

10. የክትትልና ድጋፍ ሥራ ያከናውናል፣ አጭር የስራ ግምገማ፣ ወርሃዊና በየሩብ አመቱ ለሚቀርቡ ሪፖርቶች ላይ በመመስረት ዘርዘር ያለ ግምገማ ያደርጋል። በየሩብ ዓመት ክላስተሮችንና ወረዳዎችን ናሙና በመውሰድ የታቀዱ ስራዎች እንዴት እየተከናወኑ እንዳሉ ሱፐርቪዥን ያካሄዳል፣ ይገመግማል ድጋፍ ይሰጣል።
11. የአመራርና አባላት የመደበኛ ሥራ አፈፃፀም ምዘና በመመሪያው መሰረት እንዲካሄድ ያደርጋል፣
12. ስለአፈፃፀሙም ለፓርቲው ዋና ጽ/ቤት ሪፖርት በማዘጋጀት ያቀርባል፣
13. የፌዴራል ተቋማት አስተባባሪ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለፓርቲው ዋና ጽ/ቤት ይሆናል።

## 14.የፌደራል ተቋማት አስተባባሪ ኮሚቴ አሰራር

1. በየወሩ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣
2. ምልዓተ ጉባዔው 50%+1 ነው።
3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምፅ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካል ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል። እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል።
4. የፌደራል አስተባባሪ ኮሚቴ ከክላስተር አስተባባሪ ኮሚቴ ጋር በሦስት ወር አንድ ጊዜ በእቅድ አፈፃፀም ግምገማ የጋራ ውይይት መድረክ ያካሂዳሉ።

## 15.የፌዴራል ተቋማት ክላስተር አመራር ኮሚቴ አደረጃጀት

በፌዴራል ተቋማት አደረጃጀት ሥር ሶስቱን ክላስተር /የአስተዳደር፣ የማህበራዊና የኢኮኖሚ/ የሚያስተባብሩ ሰባት አባለት ያሉ በፌዴራል ተቋማት አስተባባሪ ኮሚቴ አቅራቢነት በፓርቲ ዋና ጽ/ቤት ጸድቆ የሚመደቡ ይሆናል። ከእነዚህ መካከል ሰብሳቢ፣ 3 አባላት የፖለቲካ ንዑስ ኮሚቴ እና 3 አባላት የአደረጃጀት ንዑስ ኮሚቴ ሆኖ ተግባራትን በጋራና በተናጠል ይመሩታል።

## 16.የፌዴራል ተቋማት ክላስተር ተግባርና ኃላፊነት

1. የክላስተሩን የፖለቲካና የአደረጃጀት ሥራዎች በበላይነት ያስተባብራል፣
2. ከፌዴራል ተቋማት አስተባባሪ ኮሚቴ እቅድ መነሻ በማዘጋጀት ስራ ላይ ያውላል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል።
3. የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብ፣ መመሪያዎችና ውሳኔዎችና አቅጣጫዎችን እንዲሁም ከፌዴራል ተቋማት አስተባባሪ የሚሰጡ ተግባራትን ተግባራዊ ያደርጋል፣ ይከታተላል።

4. የክላስተሩን መረጃዎች በጥንቃቄ እንዲያዙና በአግባቡ ስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣
5. የፓርቲውን የፖለቲካ ጥራትና የስነ-ምግባር ውጤታማነት እንዲረጋገጥ አቅዶ ይሰራል፣ ይከታተላል፣
6. የውስጠ-ፓርቲ ዴሞክራሲ እንዲጎለብት በውይይቶች፣ በግምገማዎችና በክርክሮች ላይ የአባላት ተሳትፎ እንዲረጋገጥ ይሰራል፣ የአባላትን ነጻ ተሳትፎ የሚገድቡ ድርጊቶች እንዳይኖሩ ያደርጋል፣
7. ሌብነትና ብልሹ አሰራሮች ላይ ተቋማዊ በሆነ መልኩ ትግል እንዲደረግ ያደርጋል የሚፈጸሙ ጥፋቶች የፓርቲ አሰራሮች ጠብቆ የእርምት እርምጃዎች ያስወስዳል፣
8. ከክላስተሩ ኮሚሽን የሚሰጡ የኢንስፔክሽን ግኝቶች ምክረ-ሐሳቦችና ውሳኔዎችን ወስዶ ተገቢነቱን መርምሮ ተግባራዊ ያደርጋል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፣ አፈጻጸሙን ያሳውቃል፣
9. የክትትልና ድጋፍ ሥራ ያከናውናል፣ አጭር የስራ ግምገማ፣ ወርሃዊና በየሩብ አመቱ የሚቀርቡ ሪፖርቶች ላይ በመመስረት ዘርዘር ያለ ግምገማ ያደርጋል። በየሩብ ዓመቱ ወረዳዎችና የብልፅግና ህብረትን ናሙና በመውሰድ የታቀዱ ስራዎች እንዴት እየተከናወኑ እንዳሉ ሱፐርቪዥን ያካሂዳል፣ ይገመግማል ድጋፍ ይሰጣል።
10. የአመራርና አባላት የመደበኛ ሥራ አፈፃፀም ምዘና በመመሪያው መሰረት እንዲካሄድ ያደርጋል፣
11. ስለአፈፃፀሙም ለፌዴራል ተቋማት አስተባባሪ ኮሚቴ ሪፖርት በማዘጋጀት በየሩብ ዓመት ያቀርባል፣
12. የክላስተሩ አመራር ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለፌዴራል ተቋማት አስተባባሪ ኮሚቴ ይሆናል።

## 17.የፌዴራል ተቋማት ክላስተር አመራር ኮሚቴ አሰራር

1. በየሁለት ሳምንት መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣
2. ምልዓተ ጉባዔው 50%+1 ነው።
3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምፅ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50%+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካል ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል። እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል።
4. የፌደራል ተቋማት ክላስተር አመራር ኮሚቴ ከወረዳዎች አመራር ኮሚቴ ጋር በሦስት ወር አንድ ጊዜ በእቅድ አፈፃፀም ግምገማ የጋራ ውይይት መድረክ ያካሂዳሉ።

## 18.የፌዴራል ተቋማት ወረዳ አመራር አደረጃጀት

በእያንዳንዱ ክላስተር ሥር የሚገኙ ወረዳዎች በክላስተር አመራር ኮሚቴ የሚመደቡ ሰባት አባላት ባሉት የአመራር ኮሚቴ የሚመራ ይሆናል። ኮሚቴው አንድ ሰብሳቢ፣ 3 አባላት የፖለቲካ ንዑስ ኮሚቴ እና 3 አባላት የአደረጃጀት ንዑስ ኮሚቴ ይኖራቸዋል፡፡

## 19.የፌዴራል ተቋማት ወረዳ አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. የወረዳቸውን የፖለቲካና የአደረጃጀት ሥራዎች በበላይነት ያስተባብራል፤
2. የክላስተር አመራር ኮሚቴ እቅድ መነሻ በማዘጋጀት ስራ ላይ ያውላል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል።
3. የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብ፣ መመሪያዎችና ውሳኔዎችና አቅጣጫዎችን እንዲሁም ከክላስተር አመራር ኮሚቴ የሚሰጡ ተግባራትን ተግባራዊ ያደርጋል፣ ይከታተላል።
4. የወረዳውን መረጃዎች በጥንቃቄ እንዲያዙና በአግባቡ ስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣
5. የፓርቲውን የፖለቲካ ጥራትና የስነ-ምግባር ውጤታማነት እንዲረጋገጥ አቅዶ ይሰራል፣ ይከታተላል፣
6. የውስጠ-ፓርቲ ዴሞክራሲ እንዲጎለብት በውይይቶች፣ በግምገማዎችና በክርክሮች ላይ የአባላት ተሳትፎ እንዲረጋገጥ ይሰራል፣ የአባላትን ነጻ ተሳትፎ የሚገድቡ ድርጊቶች እንዳይኖሩ ያደርጋል፣
7. ሌብነትና ብልሹ አሰራሮች ተቋማዊ በሆነ መልኩ ትግል እንዲደረግ ያደርጋል የሚፈጸሙ ጥፋቶች የፓርቲ አሰራሮች ጠብቆ የእርምት እርምጃዎች ያስወስዳል፣
8. ከወረዳ ኮሚሽን የሚሰጡ የኢንስፔክሽን ግኝቶች ምክረ-ሐሳቦችና ውሳኔዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፣ የአፈጻጸሙን ያሳውቃል፣
9. የክትትልና ድጋፍ ሥራ ያከናውናል፣ አጭር የስራ ግምገማ፣ ወርሃዊና በየሩብ አመቱ ለሚቀርቡ ሪፖርቶች ላይ በመመስረት ዘርዘር ያለ ግምገማ ያደርጋል። በየሩብ አመቱ ከክላስተር አመራር ኮሚቴ ጋር መደበኛ ስብሰባ ያካሂዳል፣ በየሩብ ዓመቱ የብልፅግና ህብረትን ናሙና በመውሰድ የታቀዱ ስራዎች እንዴት እየተከናወኑ እንዳሉ ሱፐርቪዥን ያካሂዳል፣ ይገመግማል ድጋፍ ይሰጣል።
10. የአመራርና አባላት የመደበኛ ሥራ አፈፃፀም ምዘና በዓመት አንድ ጊዜና የውስጠ-ፓርቲ ምዘና በዓመት ሁለት ጊዜ እንዲካሄድ ያደርጋል፣
11. ስለአፈፃፀሙም ለክላስተር አመራር ኮሚቴ ሪፖርት በየሶስት ወሩ ያቀርባል፣
12. የወረዳ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለክላስተር አመራር ኮሚቴ ይሆናል፤

## 20. የወረዳ አመራር ኮሚቴ አሰራር

1. በየሁለት ሳምንት መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣
2. ምልዓተ ጉባዔው 50%+1 ነው።
3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምፅ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50%+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካል ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል። እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል።
4. የፌደራል ተቋማት ወረዳ አመራር ኮሚቴ ከብልፅግና ህብረት አመራር ኮሚቴ ጋር በወር አንድ ጊዜ በእቅድ አፈፃፀም ግምገማ የጋራ ውይይት መድረክ ያካሂዳሉ።

# ክፍል ሦስት

## በክልል፣ በዞን፣ በወረዳና በቀበሌ የፓርቲ አደረጃጀት፣ ተግባራት፣ ኃላፊነቶችና አሰራር

### 21.የክልል አመራር አካላት አደረጃጀት፣

በብልፅግና ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 30 እና 31 መሠረት የክልል አመራር አካላት የሚከተሉት ይሆናሉ።

1. በክልል የአስተባባሪ ኮሚቴ ፣
2. በክልል የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥራ አመራር ኮሚቴ ናቸው።

### 22.በክልል የአስተባባሪ ኮሚቴ አደረጃጀት

በክልል የአስተባባሪ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለፓርቲ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሆኖ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

1. የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር/ፕሬዝዳንት/ ................................................ ሰብሳቢ
2. በክልል የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ ........................................... ም/ሰብሳቢ
3. የክልሉ ምክትል ርዕሰ መስተዳድር/ምክትል ፕሬዝዳንት)............................... አባል
4. የክልል ም/ርዕሰ መስተዳድር /ምክትል ፕሬዝዳንት/ ማዕረግ ያሉ አመራሮች......አባላት
5. የፖለቲካ ዘርፍ ኃላፊ .........................................................................አባል
6. የአደረጃጀት ዘርፍ ኃላፊ.................................................................... አባል

### 23.በክልል የአስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. በፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 30(6) የተሰጣቸው ተግባራትና ኃላፊነቶች እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች በተጨማሪ አላቸው።
   ሀ) የምክር ቤት ዕቅድ መነሻ በማድረግ የራሱን በማዘጋጀት ተግባራዊ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ አቅጣጫ ይሰጣል፣
   ለ) የፓርቲና የመንግስት ስራዎች ተቀናጅተው እንዲተገበሩ ያደርጋል፣
   ሐ) የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ፣ መመሪያዎች፣ ውሳኔዎችና አቅጣጫዎችን ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ በአፈጻጸም የሚያጋጥሙ ችግሮችን ይለያል፣ መፍትሄ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣

መ) የፓርቲውን የፖለቲካ ጥራትና የስነ-ምግባር ውጤታማነት እንዲረጋገጥ አቅዶ ይሰራል፣ ይከታተላል፣

ሠ) ሌብነትና ብልሹ አሰራሮች ተቋማዊ በሆነ መልኩ ትግል እንዲደረግ ያደርጋል የሚፈጸሙ ጥፋቶች የፓርቲ አሰራሮች ጠብቆ የእርምት እርምጃዎች ይወስዳል፣

ረ) ከክልል ኮሚሽን የሚሰጡ የኢንስፔክሽን ግኝቶች ምክረ-ሐሳቦችና ውሳኔዎችን በመውሰድ ተገቢነቱን ምርምሮ ተግባራዊ ያደርጋል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፣ የአፈጻጸሙን ሁኔታ ያሳውቃል፣

ሰ) የክልሉን የፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ አባላት ምደባ የውሳኔ ሐሳብ ለፓርቲ ዋና ጽ/ቤት ኃላፊ ያቀርባል፣ ሲጸድቅ ያሰማራል፣ እንዲሁም የክልሉን ቀሪ አመራሮች፣ የዞን፣ ለክልል ተጠሪ የሆኑ ከተሞችና ልዩ ወረዳዎች የአስተባባሪ ኮሚቴ እና ሌሎች አመራር ምደባ ያፀድቃል፣

ሸ) የክትትልና ድጋፍ ሥራ ያከናውናል፣ ወርሃዊና በየሩብ አመቱ ለሚቀርቡ ሪፖርቶች ላይ በመመስረት ዘርዘር ያለ ግምገማ ያደርጋል፣ በየሩብ አመቱ ወይም በየስድስት ወሩ ዞኖች ናሙና በመውሰድ የታቀዱ ስራዎች እንዴት እየተከናወኑ እንዳሉ ሱፐርቪዥን ያካሂዳል፣ ይገመግማል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣

ቀ) የአመራርና የአባላት የመደበኛ ሥራ አፈፃፀም ምዘና በመመሪያው መሰረት እንዲካሄድ ያደርጋል፣

በ) በክልሉ የፓርቲውን አመራርና አባል፣ የሕዝብ፣ የተፎካካሪ ሃይሎችን ሁኔታ በዝርዝር በማወቅ እየገመገመ አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል፣

ተ) የውስጠ-ፓርቲ ዴሞክራሲ እንዲጎለብት በውይይቶች፣ በግምገማዎችና በክርክሮች ላይ የአባላት ተሳትፎ እንዲረጋገጥ ይሰራል፣ የአባላትን ነጻ ተሳትፎ የሚገድቡ ድርጊቶችን እንዳይኖሩ ያደርጋል፣

ቸ)የፓርቲ ሥራ የሚያስፈልግ የክልሉን በጀት በመመርመር የውሳኔ ሐሳብ ለፓርቲ ዋና ጽ/ቤት እንዲተላለፍ ይወስናል፣ ሲፀድቅ በአግባቡ በስራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣

ኀ) በክልል ደረጃ ጠቅላላ አመራሮች በተገኙበት የመንግስትና የፓርቲ ስራዎች መገመገሚያ መድረክ ሊካሄድ ይችላል።

2) የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ለፓርቲ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ያቀርባል።

3) ከፓርቲ ምክር ቤት እና ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚሰጡ ሌሎች ስራዎችን ያከናውናል።

## 24. በክልል የአስተባባሪ ኮሚቴ አሰራር

1. ቢያንስ በየወሩ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣
2. በየሶስት ወር የክልል ጠቅላላ የአመራር መድረክ ይካሄዳል።
3. ምልዓተ 50%+1 ነው፣
4. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን 50%+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል። እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል።

## 25. በክልል የብልፅግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥራ አመራር ኮሚቴ አደረጃጀት

በክልል የብልፅግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥራ አመራር ኮሚቴ ተጠሪነቱ በክልሉ የፓርቲው አስተባባሪ እና ለብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽ/ቤት ሆኖ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል።

1. በክልሉ የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ ............................................ ሰብሳቢ
2. ሁሉም የዘርፍ ሃላፊዎች ............................................................... አባል
3. የፓርቲ የወጣቶችና ሴቶች ክንፍ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊዎች ................ ያለድምጽ
4. ከፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሚመደብ ቃለ ጉባዔ ያዥ ........................ ያለድምጽ
5. በክልሉ የፓርቲው ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ እንደአስፈላጊነቱ በሥራ አመራር ኮሚቴው እያስወሰነ ሌሎች ኃላፊዎችን የኮሚቴው አባል ማድረግ ይችላል፣

## 26. በክልል የብልፅግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥራ አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. ከፓርቲ ዋና ጽ/ቤት የሚወርዱ ዕቅዶችን እና የአስተባባሪ ኮሚቴ ዕቅድ መነሻ በማድረግ ከራሱ ክልል ሁኔታ ጋር በማጣጣም የፖለቲካና የአደረጃጀት ስራዎችን ያቅዳል፣ ፈፃሚ አካላትን ለስራው ያዘጋጃል፣ ያሰማራል፣ የስራው ሂደትም ይከታተላል፣ ይደግፋል፣
2. የአባላት የዕለት ተዕለት ግንባታ ስራን በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት እየተከናወነ መሆኑንና በየወቅቱ ያለውን የአባላት ፖለቲካዊ ሁኔታ በመገምገም የግንባታ ስራው እያጠናከረ ይሄዳል። ጠንካራ የብልፅግና ቤተሰብና የብልፅግና ህብረት አመራር የመፍጠር ስራን ያቅዳል ተግባራዊ መሆኑንም ያረጋግጣል፣
3. በፓርቲው የሚካሄደውን የአባላትና የአመራር የስልጠና ስራ ያጠናል፣ ያቅዳል፣ ያደራጃል፣ ስልጠናውም እንዲካሄድ ያደርጋል፣
4. የፓርቲዉን የፖለቲካ፣ የአደረጃጀት፣ የባድርሻ አካላትና የኮሙኒኬሽን ስራዎች ሁኔታ ይከታተላል፣ ይለያል፣ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣

5. የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ፣ መመሪያዎች፣ ውሳኔዎችና አቅጣጫዎችን ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ በአፈጻጸም የሚያጋጥሙ ችግሮችን ይለያል፣ መፍትሄ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣
6. የፓርቲውን የፖለቲካ ጥራትና የስነ-ምግባር ውጤታማነት እንዲረጋገጥ አቅዶ ይሰራል፣ ይከታተላል፣ ያስፈጽማል፣
7. ሌብነትና ብልሹ አሰራሮች ተቋማዊ በሆነ መልኩ ትግል እንዲደረግ ያደርጋል፣ የሚፈጸሙ ጥፋቶች የፓርቲ አሰራሮች ጠብቆ የእርምት እርምጃዎች እንዲወሰድ ያደርጋል፣
8. ከክልል ኮሚሽን በሚቀርቡ የኢንስፔክሽን የጥናት ግኝቶች ምክረ ሐሳብና ውሳኔዎች በመውሰድ ተገቢነቱን መርምሮ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣አፈጻጸሙን ይከታተላል፣
9. የፓርቲ ገንዘብ፣ ንብረትና ሰነዶች በአግባቡ መያዛቸውንና ሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፣
10. የፓርቲ አባላት መወጮ እና ልዩ ልዩ ገቢዎች በፓርቲ ህጋዊ ደረሰኝ ተሰብስቦ ገቢ መሆኑን ያረጋግጣል፣
11. የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ሰራተኛ በሰው ኃይል አስተዳደር መመሪያ መሰረት መተዳደሩን ያረጋግጣል፣
12. የፓርቲ አመራርና አባል፣ የክልሉ ሕዝብ፣ የተፎካካሪዎች ፓርቲዎች ሁኔታን በየጊዜው እየተከታተለ ተገቢውን አቅጣጫ እየሰጠ ይሄዳል፣
13. በዞን/በከተማ/በልዩ ወረዳ የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤትን በቅርበት በመከታተል ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፣
14. የአመራርና የአባላት የመደበኛ ተግባርና የውስጠ ፓርቲ ተልዕኮ አፈፃፀም ምዘና በምዘና ማስፈፀሚያ መመሪያዎች መሰረት እንዲካሄድ ያደርጋል።
15. የሚከተለውን የክትትልና ድጋፍ ሥራ ያከናውናል፡- ሳምንታዊ አጭር የስራ ግምገማ፣ ወርሃዊና በየሩብ አመቱ በሚቀርቡ ሪፖርቶች ላይ በመመስረት ዘርዘር ያለ ግምገማ ይደረጋል። በክልሉ ካሉት ዞኖች በሶስት ወር ወይም በየ6 ወሩ ዞኖችንና ወረዳዎችን ናሙና በመውሰድ የታቀዱ ስራዎች እንዴት እየተከናወኑ እንዳሉ በአካል በመውረድ ያያል፣ ይገመግማል፣ ድጋፍ ይሰጣል። ከዞንና ከተሞች የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ጋር በየ3 ወሩ የስራ አፈጻጸም ግምገማ የጋራ መድረክ ይኖረዋል፣

16. በብልፅግና ፓርቲ ልሳንና በራሪ ጽሑፎች እንዲሁም መፅሔት ለሚካሄደው የአባላት ግንባታ አጀንዳዎችን በመቅረጽ ያስተላልፋል፣
17. የቅርንጫ ጽ/ቤቱን በጀት ሲፀድቅ በአግባቡ በስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣
18. የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ለክልል አስተባባሪ ኮሚቴና ለፓርቲ ዋና ጽ/ቤት በየሦስት ወሩ ያቀርባል።
19. በክልል ከአስተባባሪ ኮሚቴና ከፓርቲ ዋና ጽ/ቤት የሚሰጡ ሌሎች ስራዎችን ያከናውናል።

## 27. በክልል የብልፅግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥራ አመራር ኮሚቴ አሰራር

1. በየሁለት ሳምንቱ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣
2. ምልዓተ ጉባኤው 50%+1 ነው።
3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን 50%+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል። እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል።
4. በፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እቅድ አፈጻጸም፣ የጋራ ግንዛቤ በሚጠይቁ ጉዳዮች ላይ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ውስጥ ከሚገኙ መላው ተሿሚዎችና ዳሬክተሮች፣ ልዩ ወረዳዎችና ከተሞች የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሥራ አመራር ኮሚቴ ጋር በሦስት ወር አንድ ጊዜ በእቅድ አፈፃፀም ግምገማ የጋራ ውይይት መድረክ ያካሂዳሉ።
5. በክልል ደረጃ በክልል የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሥራ አመራር ኮሚቴ ከክልል ተጠሪ ከሆኑ ዞን/ልዩ ወረዳ/ለክልል ተጠሪ ከሆኑ ከተሞች የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሥራ አመራር ኮሚቴ ጋር በሦስት ወር አንድ ጊዜ በእቅድ አፈፃፀም ግምገማ የጋራ ውይይት መድረክ ያካሂዳሉ፣ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ባጠረ ጊዜ የጋራ መድረክ ሊካሄድ ይችላል።
6. በየክልሉ የክላስተር አወቃቀር በተመለከተ ከላይ ለፌዴራል የተቀመጠ እንደለ ሆኖ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ደቡብ ኢትዮጵያ እና ማዕከላዊ ኢትየጵያ በራሳቸው ባዋቀሩት መንግስታዊ ክላስተር የፓርቲ የአደረጃጀት ስራ የሚከናወን ይሆናል።

## 28. በዞን የአመራር አካላት አደረጃጀት

የዞን አመራር አካላት የሚከተሉት ይሆናሉ።

1. በዞኑ የአስተባባሪ ኮሚቴ እና
2. የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ ናቸው።

## 29. በዞን የአስተባባሪ ኮሚቴ አደረጃጀት

በዞን የአስተባባሪ ኮሚቴ ተጠሪነቱ በክልል ለአስተባባሪ ኮሚቴ ሆኖ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፣

1. የዞን አስተዳዳሪ /ከንቲባ/ ……………………………………………….ሰብሳቢ
2. በዞን የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ ……………………………ም/ሰብሳቢ
3. የዞን ምክትል አስተዳዳሪ/ምክትል ከንቲባ ………………………………አባል
4. የፖለቲካና አቅም ግንባታ ዘርፍ ኃላፊ …………………………………አባል
5. የአደረጃጀት ዘርፍ ኃላፊ …………………………………………………አባል

## 30. በዞን የአስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. በፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 30(6) የተሰጣቸው ተግባራትና ኃላፊነቶች እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች በተጨማሪነት አላቸው።

ሀ) በክልል የአስተባባሪ ኮሚቴ ዕቅድ መነሻ በማድረግ የራሱን በማዘጋጀት ተግባራዊ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ አቅጣጫ ይሰጣል፣

ለ) የፓርቲና የመንግስት ስራዎች ተቀናጅተው እንዲተገበሩ ያደርጋል፣

ሐ) የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ፣ መመሪያዎች፣ ውሳኔዎችና አቅጣጫዎችን ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ በአፈጻጸም የሚያጋጥሙ ችግሮችን ይለያል፣ መፍትሄ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣

መ) የፓርቲውን የፖለቲካ ጥራትና የስነ-ምግባር ውጤታማነት እንዲረጋገጥ አቅዶ ይሰራል፣ ይከታተላል፣

ሠ) ሌብነትና ብልሹ አሰራሮች ተቋማዊ በሆነ መልኩ ትግል እንዲደረግ ያደርጋል የሚፈጸሙ ጥፋቶች የፓርቲ አሰራሮች ጠብቆ የእርምት እርምጃዎች ይወስዳል፣

ረ) ከክልል ኮሚሽን በሚቀርቡ የኢንስፔክሽን የጥናት ግኝቶች ምክረ ሐሳብና ውሳኔዎች በመውሰድ ተገቢነቱን መርምሮ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ውጤቱን ያሳውቃል፣

ሰ) በዞኑ የአስተባባሪ ኮሚቴ አባላት ምደባ የውሳኔ ሐሳብ በክልል ለአስተባባሪ ኮሚቴ ያቀርባል፣ ሲጸድቅ ያሰማራል፣ እንዲሁም የዞኑን ቀሪ አመራሮች፣ ለዞን ተጠሪ የሆኑ ወረዳዎችና ከተሞች የአስተባባሪ ኮሚቴ እና ሌሎች አመራር ምደባ ያፀድቃል፣

ሸ) የክትትልና ድጋፍ ሥራ ያከናውናል፣ ወርሃዊና በየሩብ አመቱ ለሚቀርቡ ሪፖርቶች ላይ በመመስረት ዘርዝር ያለ ግምገማ ያደርጋል፣ በየሩብ አመቱ በሶስት ወር ወይም በየስድስት ወሩ ወረዳዎችንና ከተሞችን ናሙና በመውሰድ የታቀዱ ስራዎች እንዴት እየተከናወኑ እንዳሉ ሱፐርቪዥን ያካሂዳል፣ ይገመግማል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣

ቀ) የአመራርና የአባላት የመደበኛ ሥራና የውስጠ ፓርቲ ተልዕኮ አፈፃፀም ምዘና በምዘና ማስፈፀሚያ መመሪያዎች መሰረት እንዲካሄድ ያደርጋል፤

በ) በዞኑ የፓርቲውን አመራርና አባል፣ የሕዝብ፣ የተፎካካሪ ሃይሎችን ሁኔታ በዝርዝር በማወቅ እየገመገመ አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል፣

ተ) የውስጠ-ፓርቲ ዴሞክራሲ እንዲጎለብት በውይይቶች፣ በግምገማዎችና በክርክሮች ላይ የአባላት ተሳትፎ እንዲረጋገጥ ይሰራል፣ የአባላትን ነጻ ተሳትፎ የሚገድቡ ድርጊቶችን እንዳይኖሩ ያደርጋል፣

ነ) በዞን ደረጃ ጠቅላላ አመራሮች በተገኙበት የመንግስትና የፓርቲ ስራዎች መገመገሚያ መድረክ ሊካሄድ ይችላል።

2) የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት በክልል ለአስተባባሪ ኮሚቴ በየሦስት ወሩ ሪፖርት ያቀርባል።

3) በክልል ከአስተባባሪ ኮሚቴ የሚሰጡ ሌሎች ስራዎችን ያከናውናል።

## 31. በዞኑ የአስተባባሪ ኮሚቴ አሰራር

1. በየሁለት ሳምንቱ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣ ሆኖም አስቸኳይ ተግባራት ሲኖር ከተጠቀሰው ቀን ባጠረ ለስብሰባ ሊካሄድ ይችላለ።
2. በየሶስት ወር የዞን ጠቅላላ የአመራር መድረክ ይካሄዳል።
3. ምልዓተ ጉባኤው 50%+1 ነው።
4. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50%+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል። እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል።

## 32. በዞን የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥራ አመራር ኮሚቴ አደረጃጀት

በዞን የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥራ አመራር ኮሚቴ ተጠሪነቱ በዞን ለአስተባባሪ ኮሚቴና በክልል ለፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥራ አመራር ኮሚቴ ሆኖ የሚከተሉት ይሆናሉ።

1. የፓርቲ ጽ/ቤት ኃላፊ ……………………………………………………ሰብሳቢ
2. የሁሉም ዘርፍ ኃላፊ ……………………………………………………..አባል
3. የፓርቲ ወጣቶችና ሴቶች ክንፍ ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎች ……………………ያለድምጽ

4. ከፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሚመደብ ቃለ ጉባዔ ያዥ …………………ያለድምጽ
5. የፓርቲው ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ እንደአስፈላጊነቱ በአመራር ኮሚቴዉ እያስወሰነ ሌሎች የስራ ኃላፊዎችን ሊጨምር ይችላል።

## 33. በዞን የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥራ አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1) በክልል የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሚወርዱ ዕቅዶችን መነሻ በማድረግ ከራሱ ከዞኑ ሁኔታ ጋር በማጣጣም የፖለቲካና የአደረጃጀት ስራዎችን ያቅዳል፣ ፈፃሚ አካላትን ለስራው ያዘጋጃል፣ ያሰማራል፣ የስራው ሂደትም ይከታተላል፣ ይደግፋል፣
2) የአባላት የዕለት ተዕለት ግንባታ ስራን በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት እየተከናወነ መሆኑንና በየወቅቱ ያለውን የአባላት ፖለቲካዊ ሁኔታ በመገምገም የግንባታ ስራው እያጠናከረ ይሄዳል። ጠንካራ የብልፅግና ቤተሰብና የብልጽግና ህብረት አመራር የመፍጠር ስራን ያቅዳል ተግባራዊ መሆኑንም ያረጋግጣል፣
3) በፓርቲው የሚካሄደውን የአባላትና የአመራር የስልጠና ስራ ያጠናል፣ ያቅዳል፣ ያደራጃል፣ ስልጠናውም እንዲካሄድ ያደርጋል፣
4) የፓርቲዉን የፖለቲካ፣ የአደረጃጀት፣ የባድርሻ አካላትና የኮሙኒኬሽን ስራዎች ሁኔታ ይከታተላል፣ ይለያል፣ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣
5) የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ፣ መመሪያዎች፣ ውሳኔዎችና አቅጣጫዎችን ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ በአፈጻጸም የሚያጋጥሙ ችግሮችን ይለያል፣ መፍትሄ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣
6) የፓርቲውን የፖለቲካ ጥራትና የስነ-ምግባር ውጤታማነት እንዲረጋገጥ አቅዶ ይሰራል፣ ይከታተላል፣ ያስፈጽማል፣
7) ሌብነትና ብልሹ አሰራሮች ተቋማዊ በሆነ መልኩ ትግል እንዲደረግ ያደርጋል፣ የሚፈጸሙ ጥፋቶች የፓርቲ አሰራሮች ጠብቆ የእርምት እርምጃዎች እንዲወሰድ ያደርጋል፣
8) ከዞን ኮሚሽን በሚቀርቡ የኢንስፔክሽን የጥናት ግኝቶች ምክረ ሐሳብና ውሳኔዎች በመውሰድ ተገቢነቱን መርምሮ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ውሳኔውን ያሳውቃል፣
9) የፓርቲ ገንዘብ፣ ንብረትና ሰነዶች በአግባቡ መያዛቸውንና ሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፣
10) የፓርቲ አባላት መዋጮ እና ልዩ ልዩ ገቢዎች በፓርቲ ህጋዊ ደረሰኝ ተሰብስቦ ገቢ መሆኑን ያረጋግጣል፣

11) የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ሰራተኛ በሰው ኃይል አስተዳደር መመሪያ መሰረት መተዳደሩን ያረጋግጣል፣

12) የፓርቲ አመራርና አባል፣ የክልሉ ሕዝብ፣ የተፎካካሪዎች ፓርቲዎች ሁኔታን በየጊዜው እየተከታተለ ተገቢውን አቅጣጫ እየሰጠ ይሄዳል፣

13) በወረዳና በከተማ የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤትን በቅርበት በመከታተል ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፣

14) የአመራርና የአባላት የመደበኛ ተግባር አፈፃፀም ምዘና በዓመት አንድ ጊዜ እና የውስጠ-ፓርቲ ምዘና በዓመት ሁለት ጊዜ እንዲካሄድ ያደርጋል፣

15) ሳምንታዊ አጭር የስራ ግምገማ፣ ወርሃዊና በየሩብ አመቱ ለሚቀርቡ ሪፖርቶች ላይ በመመስረት ዘርዘር ያለ ግምገማ ይደረጋል። በዞኑ ካሉት ወረዳዎችና ከተሞች በሶስት ወር ወይም በየ6 ወሩ ናሙና በመውሰድ የታቀዱ ስራዎች እንዴት እየተከናወኑ እንዳሉ በአካል በመውረድ ያያል፣ ይገመግማል፣ ድጋፍ ይሰጣል። በወረዳና በከተሞች የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ጋር በየ3 ወሩ የስራ አፈጻጸም ግምገማ የጋራ መድረክ ይኖረዋል፣

16) በብልፅግና ፓርቲ ልሳንና በራሪ ጽሑፎች እንዲሁም መፅሔት ለሚካሄደው የአባላት ግንባታ አጀንዳዎችን በመቅረጽ ያስተላልፋል፣

17) የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት በዞን ለአስተባባሪ ኮሚቴና በክልል ለፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በየሦስት ወሩ ያቀርባል።

18) በዞን ከአስተባባሪ ኮሚቴና በክልል ከፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሚሰጡ ሌሎች ስራዎችን ያከናውናል።

## 34. በዞን የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥራ አመራር ኮሚቴ አሰራር

1. በየሁለት ሳምንቱ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣
2. ምልዓተ ጉባኤው 50%+1 ነው።
3. ውሳኔዎች በተባባረ ድምጽ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50%+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል። እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል።
4. በፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እቅድ አፈጻጸም፣ የጋራ ግንዛቤ መያዝ እና መግባባት በሚጠይቁ ጉዳዮች ላይ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ውስጥ ከሚገኙ መላው ተሿሚዎችና ዳይሬክተሮች ጋር በየሦስት ወሩ የጋራ የውይይት መድረክ ይካሄዳል።

5. በዞን ደረጃ በዞን የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ ለዞን ተጠሪ ከሆኑ በወረዳዎችና በከተሞች የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሥራ አመራር ኮሚቴ ጋር በሦስት ወር አንድ ጊዜ በእቅድ አፈፃፀም ግምገማ የጋራ ውይይት መድረክ ያካሂዳሉ ፣ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ባጠረ ጊዜ ግምገማ ሊያካሄድ ይችላል።

## 35.በወረዳ የአመራር አካላት አደረጃጀት

በወረዳ የአመራር አካላት የሚከተሉት ይሆናሉ።

1. በወረዳው የአስተባባሪ ኮሚቴ እና
2. በወረዳው የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥራ አመራር ኮሚቴ ናቸው።

## 36.በወረዳ የአስተባባሪ ኮሚቴ አደረጃጀት

በወረዳ የአስተባባሪ ኮሚቴ ተጠሪነቱ በዞን ለአስተባባሪ ኮሚቴ ሆኖ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፣

1. የወረዳ አስተዳዳሪ ……………………………………………………ሰብሳቢ
2. የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ ………………………………………ም/ሰብሳቢ
3. የወረዳ ምክትል አስተዳዳሪ ……………………………………………….አባል
4. የፖለቲካና አቅም ዘርፍ ኃላፊ …………………………………………….አባል
5. የአደረጃጀት ዘርፍ ኃላፊ ………………………………………………….አባል

## 37.በወረዳ የአስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. በፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 30(6) የተሰጣቸው ተግባራትና ኃላፊነቶች እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች በተጨማሪ አላቸው።

   ሀ) በዞን የአስተባባሪ ኮሚቴ ኮሚቴ ዕቅድ መነሻ በማድረግ የራሱን በማዘጋጀት ተግባራዊ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ አቅጣጫ ይሰጣል፣

   ለ) የፓርቲና የመንግስት ስራዎች ተቀናጅተው እንዲተገበሩ ያደርጋል፣

   ሐ) የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ፣ መመሪያዎች፣ ውሳኔዎችና አቅጣጫዎችን ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ በአፈጻጸም የሚያጋጥሙ ችግሮችን ይለያል፣ መፍትሄ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣

   መ) የፓርቲውን የፖለቲካ ጥራትና የስነ-ምግባር ውጤታማነት እንዲረጋገጥ አቅዶ ይሰራል፣ ይከታተላል፣

ሠ) ሌብነትና ብልሹ አሰራሮች ተቋማዊ በሆነ መልኩ ትግል እንዲደረግ ያደርጋል የሚፈጸሙ ጥፋቶች የፓርቲ አሰራሮች ጠብቆ የእርምት እርምጃዎች ይወስዳል፣

ረ) ከወረዳ ኮሚሽን በሚቀርቡ የኢንስፔክሽን የጥናት ግኝቶች ምክረ ሐሳብና ውሳኔዎች በመውሰድ ተገቢነቱን መርምሮ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣አፈጻጸሙን በመከታተል ያሳውቃል፣

ሰ) በወረዳ የአስተባባሪ ኮሚቴ አባላት ምደባ የውሳኔ ሐሳብ በዞን ለአስተባባሪ ኮሚቴ ያቀርባል፣ ሲጸድቅ ያሰማራል፣ እንዲሁም የወረዳውን ቀሪ አመራሮች፣ የቀበሌ የአስተባባሪ ኮሚቴ እና ሌሎች አመራር ምደባ ያፀድቃል፣

ሸ) የክትትልና ድጋፍ ሥራ ያከናውናል፣ ወርሃዊና በየሩብ አመቱ ለሚቀርቡ ሪፖርቶች ላይ በመመስረት ዘርዘር ያለ ግምገማ ያደርጋል፣ በየሩብ አመቱ ወይም በየስድስት ወሩ የቀበሌና የብልፅግና ህብረት ናሙና በመውሰድ የታቀዱ ስራዎች እንዴት እየተከናወኑ እንዳሉ ሱፐርቪዥን ያካሄዳል፣ ይገመግማል፣ ድጋፍ ይሰጣል፣

ቀ) የአመራርና የአባላት የመደበኛ ሥራ አፈፃፀም ምዘና በመመሪያው መሰረት እንዲካሄድ ያደርጋል፣

በ) የወረዳውን የፓርቲውን አመራርና አባል፣ የሕዝብ፣ የተፎካካሪ ሃይሎችን ሁኔታ በዝርዝር በማወቅ እየገመገመ አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል፣

ተ) የውስጠ-ፓርቲ ዴሞክራሲ እንዲጎለብት በውይይቶች፣ በግምገማዎችና በክርክሮች ላይ የአባላት ተሳትፎ እንዲረጋገጥ ይሰራል፣ የአባላትን ነጻ ተሳትፎ የሚገድቡ ድርጊቶችን እንዳይኖሩ ያደርጋል፣

ነ) በወረዳ ደረጃ ጠቅላላ አመራሮች በተገኙበት የመንግስትና የፓርቲ ስራዎች መገማገሚያ መድረክ ሊካሄድ ይችላል።

2. የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት በዞን ለአስተባባሪ ኮሚቴ በየሶስት ወሩ ሪፖርት ያቀርባል።
3. በዞን ከአስተባባሪ ኮሚቴ የሚሰጡ ሌሎች ስራዎችን ያከናውናል።

## 38. በወረዳ የአስተባባሪ ኮሚቴ አሰራር

1. በየሁለት ሳምንቱ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል።
2. በየሶስት ወር የወረዳ ጠቅላላ የአመራር መድረክ ይካሄዳል።
3. ምልዓተ ጉባኤው 50%+1 ነው።

4. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50%+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል። እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል።

## 39.በወረዳ የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥራ አመራር ኮሚቴ አደረጃጀት

በወረዳ የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥራ አመራር ኮሚቴ ተጠሪነቱ በወረዳ ለአስተባባሪ ኮሚቴና በዞን ለፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥራ አመራር ኮሚቴ ሆኖ የሚከተሉት አባላት ይሆናሉ።

1. የፓርቲ ጽ/ቤት ኃላፊ ………………………………………………………ሰብሳቢ
2. የዘርፍ ኃላፊዎች ………………………………………………………...አባል
3. የፓርቲ ወጣቶችና ሴቶች ክንፍ ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎች …………………ያለድምጽ
4. ከፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሚመደብ ቃለ ጉባዔ ያዥ ……………...ያለድምጽ
5. የፓርቲው ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ እንደአስፈላጊነቱ በአመራር ኮሚቴዉ እያስወሰነ ሌሎች የስራ ኃላፊዎችን ሊጨምር ይችላል።

## 40.በወረዳ የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ስራ አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1) በዞን ከፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሚወርዱ ዕቅዶችን መነሻ በማድረግ የራሱን የፖለቲካና የአደረጃጀት ስራዎችን ያቅዳል፣ ፈፃሚ አካላትን ለስራው ያዘጋጃል፣ ያሰማራል፣ የስራው ሂደትም ይከታተላል፣ ይደግፋል፣
2) የአባላት የዕለት ተዕለት ግንባታ ስራን በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት እየተከናወነ መሆኑንና በየወቅቱ ያለውን የአባላት ፖለቲካዊ ሁኔታ በመገምገም የግንባታ ስራው እያጠናከረ ይሄዳል።
3) በፓርቲው የሚካሄደውን የአባላትና የአመራር የስልጠና ስራ ያጠናል፣ ያቅዳል፣ ያደራጃል፣ ስልጠናውም እንዲካሄድ ያደርጋል፣
4) የፓርቲዉን የፖለቲካ፣ የአደረጃጀት፣ የባድርሻ አካላትና የኮሙኒኬሽን ስራዎች ሁኔታ ይከታተላል፣ ይለያል፣ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣
5) የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ፣ መመሪያዎች፣ ውሳኔዎችና አቅጣጫዎችን ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ በአፈጻጸም የሚያጋጥሙ ችግሮችን ይለያል፣ መፍትሄ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣
6) የፓርቲውን የፖለቲካ ጥራትና የስነ-ምግባር ውጤታማነት እንዲረጋገጥ አቅዶ ይሰራል፣ ይከታተላል፣ ያስፈጽማል፣

7) ሌብነትና ብልሹ አሰራሮች ተቋማዊ በሆነ መልኩ ትግል እንዲደረግ ያደርጋል፣ የሚፈጸሙ ጥፋቶች የፓርቲ አሰራሮች ጠብቆ የእርምት እርምጃዎች እንዲወሰድ ያደርጋል፣

8) ከወረዳ ኮሚሽን በሚቀርቡ የኢንስፔክሽን የጥናት ግኝቶች ምክረ ሐሳብና ውሳኔዎች በመውሰድ ተገቢነቱን መርምሮ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል፣አፈጻጸሙን በመከታተል ያሳውቃል፣

9) የፓርቲ ገንዘብ፣ ንብረትና ሰነዶች በአግባቡ መያዛቸውንና ሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፣

10) የፓርቲ አባላት መወጮ እና ልዩ ልዩ ገቢዎች በፓርቲ ህጋዊ ደረሰኝ ተሰብስቦ ገቢ መሆኑን ያረጋግጣል፣

11) የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ሰራተኛ በሰው ኃይል አስተዳደር መመሪያ መሰረት መተዳደሩን ያረጋግጣል፣

12) የፓርቲ አመራርና አባል፣ የክልሉ ሕዝብ፣ የተፎካካሪዎች ፓርቲዎች ሁኔታን በየጊዜው እየተከታተለ ተገቢውን አቅጣጫ እየሰጠ ይሄዳል፣

13) በቀበሌ የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤትን በቅርበት በመከታተል ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፣

14) የአመራርና የአባላት የመደበኛ ተግባር አፈፃፀም ምዘና በመመሪያው መሰረት እንዲካሄድ ያደርጋል፣

15) ሳምንታዊ አጭር የስራ ግምገማ፣ ወርሃዊና በየሩብ አመቱ ለሚቀርቡ ሪፖርቶች ላይ በመመስረት ዘርዘር ያለ ግምገማ ይደረጋል። ከቀበሌዎች ጋር በየሩብ ዓመት ብልፅግና ህብረት ናሙና በመውሰድ ሱፐርቪዥን ያደርጋል፣ ግብረ መልስ ይሰጣል። በቀበሌ ከፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ጋር በየ3 ወሩ የስራ አፈጻጸም ግምገማ የጋራ መድረክ ይኖረዋል፣

16) በብልፅግና ፓርቲ ልሳንና በራሪ ጽሑፎች እንዲሁም መፅሔት ለሚካሄደው የአባላት ግንባታ አጀንዳዎችን በመቅረጽ ያስተላልፋል፣

17) የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት በወረዳ ለአስተባባሪ ኮሚቴና በዞን ለፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በየሦስት ወሩ ያቀርባል።

18) በወረዳ ከአስተባባሪ ኮሚቴ እና በዞን ከፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሚሰጡ ሌሎች ስራዎችን ያከናውናል።

## 41. በወረዳ የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ አሰራር

1. በየሁለት ሳምንቱ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣ ሆኖ ባጠረ ጊዜ ስብሰባ ሊያካሄድ ይችላል።
2. ምልዓተ ጉባኤው 50%+1 ነው።
3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50%+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል። እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል።
4. በፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እቅድ እና አፈጻጸም፣ የጋራ ግንዛቤ በሚጠይቁ ጉዳዮች ላይ በፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ውስጥ ከሚገኙ መላው ተሿሚዎችና ምድብተኞች ጋር በየሦስት ወሩ የጋራ የውይይት መድረክ ይካሄዳል። እንደአስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።
5. በወረዳ ደረጃ በወረዳ የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ ለወረዳ ተጠሪ ከሆኑ በቀበሌዎች የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሥራ አመራር ኮሚቴ ጋር በሦስት ወር አንድ ጊዜ በእቅድ አፈፃፀም ግምገማ የጋራ ውይይት መድረክ ያካሂዳሉ።እንደአስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።

## 42. በቀበሌ የአመራር አካላት አደረጃጀት

በቀበሌ የአመራር አካላት የሚከተሉት ይሆናሉ።

1. በቀበሌ የአስተባባሪ ኮሚቴ እና
2. የፓርቲ ጽ/ቤት ሥራ አመራር ኮሚቴ

## 43. በቀበሌ የአስተባባሪ ኮሚቴ አደረጃጀት

1) በቀበሌ የፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ ተጠሪነቱ በከተማ/በወረዳ/በልዩ ወረዳ/ የፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ ሆኖ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፣
   1. የቀበሌ አስተዳዳሪ ....................................................................ሰብሳቢ
   2. የቀበሌ ም/አስተዳዳሪ .................................................................. አባል
   3. በቀበሌ የፓርቲ ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊ ወይም አንድ የህብረት ሰብሳቢ................ም/ሰብሳቢ
   4. ሌሎች ቀሪ የብልፅግና ህብረት ሰብሳቢ/ሰብሳቢዎች .................................. አባል
   5. የቀበሌ ስራ አስኪያጅ .............................................................. ያለድምጽ
   6. ሴቶች ክንፍ ሰብሳቢ................................................................ ያለድምጽ
   7. ወጣት ክንፍ ሰብሳቢ................................................................ ያለድምጽ

2) በቀበሌ የፓርቲ ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊ ከሌለ የአስተባባሪ ምክትል ሰብሳቢ ካሉ የብልፅግና ህብረት ሰብሳቢ አመራሮች መካከል በድምፅ ይመረጣል። ሌሎች የህብረቱ ሰብሳቢ/ሰብሳቢዎች አባል ይሆናሉ።

## 44. በቀበሌው የአስተባባሪ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. በወረዳ/ልዩ ወረዳ/ከተማ ከአስተባባሪ ኮሚቴ እቅድ መሰረት የቀበሌውን የፖለቲካ ስራና የመንግስት ስራዎች የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ያቅዳል፣ ይፈጽማል፣ይከታተላል፣
2. በቀበሌ የፓርቲና የመንግስት ስራዎች ተቀናጅተው እንዲተገበሩ ያደርጋል፣ ይገመግማል፣
3. የፓርቲዉን የፖለቲካ፣ የድርጅት፣ የባድርሻ አካላትና የኮሙኒኬሽን ስራዎች ሁኔታ ይከታተላል፣ ይለያል፣ ይገመግማል፣
4. የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ፣ መመሪያዎች፣ የተቀመጡ አቅጣጫዎች በቀበሌ ውስጥ በአግባቡ ስራ ላይ ያውላል፣ ይከታተላል፣ ይገመግማል።
5. የፓርቲውን የፖለቲካ ጥራትና የስነ-ምግባር ውጤታማነት የሚያረጋግጡ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን አቅዶ ይሰራል፣ ይከታተላል፣ ያስፈጽማል፣
6. የውስጠ-ፓርቲ ዴሞክራሲ እንዲጎለብት በውይይቶች፣ በግምገማዎችና በክርክሮች ላይ የአባላት ተሳትፎ እንዲረጋገጥ ይሰራል፣ የአባላትን ነጻ ተሳትፎ የሚገድቡ ድርጊቶችን እንዳይኖሩ ያደርጋል፣
7. ሌብነትና ብልሹ አሰራሮች የብልፅግና ቤተሰብና የብልፅግና ህብረት አጀንዳ ሆነው በዕቅድ ተይዘው ትግል እንዲደረግ ያደርጋል፣ ጥፋቶች ሲፈጸሙ እርምጃዎችን እንዲወሰድ ያደርጋል፣
8. ከቀበሌ ኮሚሽን የሚሰጡ የኢንስፔክሽን ግኝቶች ምክረ-ሐሳቦችና ውሳኔዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፣ የአፈጻጸሙን ያሳውቃል፣
9. የፓርቲ አባላት መዋጮና የድጋፌ ገቢ በአግባቡ በህጋዊ ደረሰኝ ተሰብስቦ ለወረዳ ገቢ እንዲሆን ያደርጋል፣
10. ለብልፅግና ህብረትና ለብልፅግና ቤተሰብ አመራር አካላትን በቅርብ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል።
11. በቀበሌ የፓርቲ አስተባባሪ እና በቀበሌ የአመራር ምደባ የውሳኔ ሀሳብ ቀጥሎ ላለው በወረዳ/ልዩ ወረዳ/ከተማ የአስተባባሪ ኮሚቴ ያቀርባል፣ ሲጸድቅ ያሰማራል፣
12. የቀበሌውን የአባላት፣ የአመራር፣ የሕዝብ፣ የተፎካካሪ ፓርቲዎች ሁኔታን በዝርዝር እየገመገመ በወረዳ ለአስተባባሪ ኮሚቴ ያቀርባል፣
13. የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት በወረዳ ለአስተባባሪ ኮሚቴ በየሦስት ወሩ ያቀርባል።

14. ከአስተባባሪ ኮሚቴ ሰብሳቢ የሚሰጡ ሌሎች ስራዎችን ያከናውናል።

## 45. በቀበሌ የአስተባባሪ ኮሚቴ አሰራር

1. በየሁለት ሳምንቱ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል።
2. ምልዓተ ጉባዔው 50%+1 ነው።
3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምጽ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50%+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል። እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል።

## 46. በቀበሌ የብልፅግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥራ አመራር ኮሚቴ አደረጃጀት

1) በቀበሌ የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ስራ አመራር ኮሚቴ ተጠሪነት በቀበሌው ለአስተባባሪና በወረዳ ለፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሆኖ አባላት የሚከተሉት ይሆናሉ።
   1. በቀበሌ የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ ወይም የተመረጠ …………………. ሰብሳቢ
   2. በቀበሌ የብልፅግና ህብረት ሰብሳቢ ………………………………………… ም/ሰብሳቢ
   3. በቀበሌ የብልፅግና ህብረት ሰብሳቢ………………………………………. አባል/አባላት
   4. በቀበሌ የብልፅግና ህብረት የፖለቲካ ኃላፊ ………………………….... አባል/አባላት/
   5. በቀበሌ የብልፅግና ህብረት የአደረጃጀት ኃላፊ ……………….............. አባል/አባላት
   6. በፓርቲው የወጣቶችና ሴቶች ክንፎች ………………….ያለድምጽ ተሳታፊ ይሆናሉ።
2) በቀበሌ የብልፅግና ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ የሚሆነው የየህብረቱ ሰብሳቢዎች አንድ ላይ በመሆን ከመካከላቸው የተሻለ አመራር በድምጽ ብልጫ የሚመርጡ ይሆናል። ሌሎቹ የኮሚቴ አባላት ይሆናሉ።

## 47. በቀበሌው የብልፅግና ፓርቲ ቅ/ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. በወረዳ ከፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሚወርዱ ዕቅዶችን መነሻ በማድረግ የራሱን እቅድ ያቅዳል፣ ፈፃሚ አካላትን ለስራው ያዘጋጃል፣ ያሰማራል፣ የስራው ሂደትም ይከታተላል፣ ይደግፋል፣
2. የአባላት የዕለት ተዕለት ግንባታ ስራን በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት እየተከናወነ መሆኑንና በየወቅቱ ያለውን የአባላት ፖለቲካዊ ሁኔታ በመገምገም የግንባታ ስራው እያጠናከረ ይሄዳል።
3. የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ፣ መመሪያዎች የተሰጡ አቅጣጫዎችን ሥራ ላይ ያውላል፣

4. የውስጠ-ፓርቲ ዴሞክራሲ እንዲጎለብት በውይይቶች፣ በግምገማዎችና በክርክሮች ላይ አባላት ነጻ ሆነው እንዲሳተፉ ያደርጋል፣
5. ሊብነትና ብልሹ አሰራሮች ተቋማዊ በሆነ መልኩ ትግል እንዲደረግ ያደርጋል፣ የሚፈጸሙ ጥፋቶች የፓርቲ አሰራሮች ጠብቆ የእርምት እርምጃዎች እንዲወሰድ ያደርጋል፣
6. የፓርቲ ገንዘብ፣ ንብረትና ሰነዶች በአግባቡ መያዛቸውንና ሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፣
7. የአባላት ወርሃዊ ክፍያ በፓርቲ ህጋዊ ደረሰኝ እንዲሰበሰብ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፣ በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ገቢ መሆኑን ይከታተላል፣
8. የፓርቲ አመራርና አባል፣ የቀበሌ ሕዝብ፣ የተፎካካሪዎች ፓርቲዎች ሁኔታን በየጊዜው እየተከታተለ ለሚመለከተው ክፍል ሪፖርት ያደርጋል፣
9. የብልፅግና ቤተሰብ እና የብልፅግና ህብረት እንቅስቃሴ በቅርበት ይከታተላል፣ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፣ የመሰብሰቢያ ቦታዎችን ያመቻቻል።
10. የአመራርና የአባላት የመደበኛ ተግባርና የውስጠ-ፓርቲ ተልዕኮ አፈፃፀም ምዘና በምዘና ማስፈፀሚያ መመሪያዎቹ መሰረት እንዲካሄድ ያደርጋል፣
11. ከቀበሌ ኮሚሽን በሚቀርቡ የኢንስፔክሽን ግኝቶች ምክረ ሐሳብና ውሳኔዎች እንዲሁም አፈጻጸማቸው ዙሪያ በአሰራር በተቀመጠው የግንኙነት ጊዜ በጋራ የውይይት መድረክ በመፍጠር ውይይት ያደርጋሉ፣
12. ሳምንታዊ አጭር የስራ ግምገማ፣ ወርሃዊና በየሩብ አመቱ ለሚቀርቡ ሪፖርቶች ላይ በመመስረት ዘርዘር ያለ ግምገማ ይደረጋል። የብልፅግና ቤተሰብ እና ብልፅግና ህብረት ኮሚቴ ጋር በየ3 ወሩ የስራ አፈጻጸም ግምገማ የጋራ መድረክ ይኖረዋል፣
13. የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት በቀበሌ ለአስተባባሪ ኮሚቴና በወረዳ ለፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በየሦስት ወሩ ያቀርባል።
14. የአባላትና አመራር መረጃ ያደራጃል፣ በአግባቡ ይይዛል፣ በተጨማሪ የፓርቲ ሰነዶችን በአግባቡ አደራጅቶ ይይዛል።
15. በቀበሌ ከአስተባባሪና በወረዳ ከፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኮሚቴ የሚሰጡ ሌሎች ስራዎችን ያከናውናል።

## 48.በቀበሌው የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ አሰራር

1. በየሁለት ሳምንት መደበኛ ስብሰባ ያካሂዳል።
2. ምልዓተ ጉባዔው 50%+1 ነው።

3. ውሳኔዎች በተባበረ ድምፅ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50%+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል። እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል።

4. በቀበሌ ደረጃ በቀበሌ የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አመራር ኮሚቴ ለቀበሌ ተጠሪ ከሆኑ የብልፅግና ህብረት አመራር ኮሚቴ ጋር በሦስት ወር አንድ ጊዜ የጋራ ውይይት መድረክ ያካሂዳሉ፣ ሆኖም አስቸኳይ ተግባራት ሲኖሩ ባጠረ ጊዜ ውይይት ሊያካሄድ ይችላል።

# ክፍል አራት

# የብልፅግና ህብረት፣ የብልፅግና ቤተሰብና የፓርቲ ደጋፊ አባልና ግለሰብ አደረጃጀት፣ ተግባርና ኃላፊነትና አሠራር

## 49. የብልፅግና ህብረት አደረጃጀት

1. የብልፅግና ህብረት ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ የብልፅግና ቤተሰብ በሚገኙበት ከ22 እስከ 210 የአባላት ቁጥር ይዞ የሚደራጅ ይሆናል፤
2. የብልፅግና ህብረት የሚከተሉት ተግባራትና ኃላፊነቶች ይኖሩታል።
   ሀ) የብልፅግና ህብረት አባላት በሙሉ የፓርቲ ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብ፣ መመሪያዎች፣ ውሳኔዎችና አቅጣጫዎች ላይ የተሟላ ግንዛቤ እንዲይዙ እንዲሁም የፓርቲና የመንግስት እቅዶች እንዲሳኩ እና ለተግባራዊነታቸው በግንባር ቀደምትነት የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያበቃል፣
   ለ) የውስጠ-ፓርቲ ዴሞክራሲ፣ አንድነት፣ ጥራትና ጥንካሬ ለማጎልበት የፓርቲውን ፅሳቤዎች ለመጠበቅ ሁሉም አባላት ሙሉ ተሳትፎ ማድረጋቸውን ያረጋግጣል፣
   ሐ) የብልፅግና ህብረት አባላት የፓርቲውን የአሰራሮችና የሥነ-ምግባር ሕጎች እንዲያከብሩ፣ የፓርቲውን ጥንካሬ ከሚጎዱ ማንኛውም ዝንባሌዎችና ድርጊቶች እንዲሁም ከሌብነትና ብልሹ አሰራር ነጻ ሆነው ሌሎችን እንዲያርሙ ወይም በማጋለጥ ተጠያቂ እንዲሆኑ ያደርጋል፣
   መ) የውስጠ-ፓርቲ ዴሞክራሲ እንዲጎለብት በውይይቶች፣ በግምገማዎችና በክርክሮች ላይ አባላት ነጻ ሆነው እንዲሳተፉ ያደርጋል፣ የአባላትን ነጻ ተሳትፎ የሚገድቡ ድርጊቶችን እንዳይኖሩ ያደርጋል፣
   ሠ) የፓርቲዉን የፖለቲካ፣ የአደረጃጀት፣ የፋይናንስና የኮሙኒኬሽን ስራዎች ሁኔታ ይከታተላል፣ ይገመግማል፣
   ሠ) በመተዳደሪያ ደንብ እና የአሰራር መመሪያዎች መሠረት የዕጩ አባላት ወደ ሙሉ አባልነት የመሸጋገሪያ የውሳኔ ሐሳብ ላይ ተወያይቶ በማጽደቅ ይወስናል፣
   ረ) የብልፅግና ህብረት አመራር ኮሚቴና የኮሚሽን አባላትን ይመርጣል፣ የአባላት እግድና ስንብት ላይ ውሳኔ ይሰጣል፣
   ሰ) የብልፅግና ህብረት አመራር ኮሚቴና ኮሚሽን የሚቀርበለትን እቅድና ሪፖርት ይገመግማል፣ ያጸድቃል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣

ሸ) የብልፅግና ህብረት አባላት በሙሉ በመተዳደሪያ የተቀመጡ ግዴታዎችን መወጣታቸውን ያረጋግጣል፣

ቀ) በአባላት ላይ የሚወሰዱ የሥነ-ምግባር ጥሰት የእርምት እርምጃዎች የፓርቲውን የዲሲፕሊን መመሪያ መሰረት መሆኑንና ለሌሎች አስተማሪ መሆኑን ይከታታላል፣ ያረጋግጣል፣ የውሳኔ ሃሳብ ያጸድቃል፣

በ) ሁሉም የፓርቲ አባላትና አመራር በብልፅግና ቤተሰብ መደራጀታቸውን በመፈተሽ ያረጋግጣል፣

ተ) ለብልፅግና ህብረት አባላት አቅም መገንቢያና ተሞክሮ መለዋወጫ መድርክ ሆኖ ያገለግላል።

3. በየደረጃው የሚገኙ የሴክተር መስሪያ ቤቶች በሦስት ክላስተሮች ማለትም በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በአስተዳደር ይደራጃሉ። እያንዳንዱን ክላስተር የሚመሩ አምስት አምስት አባላት ያሉት የአመራር ኮሚቴ ይኖራቸዋል። አደረጃጀቱ ተጠሪነቱ በየደረጃው ላለው የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ይሆናል። ይህንን አደረጃጀት የዕለት ተዕለት የክትትልና ድጋፍ ስራ የሚያከናውኑ አንድ አመራር በቋሚነት ተጠሪ ከሆነለት ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የሚመደብ ይሆናል።

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከአንድ በላይ የክልል መቀመጫ ከተማ ያላቸው ክልሎች በየከተሞቹ ራሳቸውን በቻሉ ክላስተሮች ሊደራጁ ይችላሉ።

## 50. የብልፅግና ህብረት የአመራር ኮሚቴ

1. ተጠሪነቱ የብልፅግና ህብረት ኮንፈረንስ እና በወረዳ/ቀበሌ/ከተማ ለአመራር ኮሚቴ የሆነ የብልፅግና ህብረት አመራር ኮሚቴ አባላት ቁጥራቸው ከ10 እስከ 12 የሆኑ በአባላት ኮንፈረንስ በሚመረጡ ይሆናል፣
2. የተመረጡ የኮሚቴ አባላት በኮንፈረንስ አባላት ፊት ቃለ መሃላ ይፈጽማሉ።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚመረጡ የአመራር ኮሚቴ አባላት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርባቸዋል።

   ሀ. በተሰማሩበት የስራ መስክ ባስመዘገበው የስራ ውጤት ለሌሎች አርአያ የሆነ፣

   ለ. በሙያውና በሥነ-ምግባሩ ምስጉን የሆነና የተሰጠውን ተልዕኮ በብቃት የሚወጣ፣

   ሐ. የፓርቲውን ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብ እና የአሰራር መመሪያዎች የተሟላ እውቀት ያለውና ለተግባራዊነታቸው በአርአያነት የሚታገል፣

መ. በሌሎች የልማትና የመልካም አስተዳደር እንቅስቃሴዎች ዙሪያ ጉልህ አስተዋጽኦ ያበረከተ፣

ሠ. በአባላትና በአካባቢው ሕብረተሰብ ዘንድ በስራው፣ በሥነ-ምግባሩና በማሕበራዊ ግንኙነቱ ተቀባይነት ያተረፈ፣

4. የብልፅግና ህብረት አመራር ኮሚቴ የራሱን ሰብሳቢ፣ ፖለቲካ ሥራዎች ኃላፊ፣ አደረጃጀት ሥራዎች ኃላፊና ፋይናንስ ሥራዎች ኃላፊ ይመረጣል።

5. የብልፅግና ህብረት አመራር ኮሚቴ በስሩም የሚከተሉት ንዑሳን ኮሚቴዎች ይኖሩታል።

ሀ. የፖለቲካ ስራዎች ንኡስ ኮሚቴ

ለ. የአደረጃጀት ስራዎች ንኡስ ኮሚቴ እና

ሐ. የፋይናንስ ሥራዎች ንኡስ ኮሚቴ ናቸው።

6. የብልፅግና ህብረት አመራር ምርጫ በየዓመቱ በማጠቃለያ በሚካሄደው የአባላት ኮንፈረንስ ይሆናል፣ ይህ እንደተጠበቀው ሆኖ የአመራር መጓደለ ካለ በየሩብ ዓመቱ በሚደረገው የአባላት ኮንፈረንስ የሚመረጡ ይሆናል።

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የብልፅግና ህብረት አባላት 22 ብቻ በሚሆኑበት ጊዜ የብልፅግና ህብረት አመራር ኮሚቴ ከብልፅግና ቤተሰብ አመራር ኮሚቴ ጨምሮ ሰባት አባላት እና የኮሚሽን ደግሞ ሶስት አባላት እንዲመረጡ ይደረጋል።

## 51. የብልፅግና ህብረት አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. የብልፅግና ህብረት የአባላት ኮንፈረንስ የፀደቀውን ዕቅድ ዝርዝር አፈፃፀም በማዘጋጀት ይፈፅማል፣ ያስፈፅማል፣

2. በልማት፣ በመልካም አስተዳደርና በፖለቲካ ስራዎች ያሉትን መልካም ልምዶች በእያንዳንዱ አባልና መዋቅራቸው ደረጃ የማስፋት ስራ በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት መከናወኑ ያረጋግጣል፣

3. የብልፅግና ህብረት አባላትን ፖለቲካዊ ጥራት፣ ጥንካሬ፣ አንድነትና አቅም እንዲጎለብት በሴሚናሮችና በግምገማ ነክ ስልጠናዎች በቀጣይነት የመገንባት ስራ ይሰራል፣

4. የብልፅግና ህብረት አባላት የፓርቲውን የአሰራሮችና የሥነ-ምግባር ሕጎች እንዲያከብሩ፣ የፓርቲውን ጥንካሬ ከሚጎዱ ማንኛውም ዝንባሌዎችና ድርጊቶች እንዲሁም ከሌብነትና ብልሹ አሰራር ነጻ ሆነው ሌሎችን እንዲያርሙ ያደርጋል፣

5. የውስጠ-ፓርቲ ዴሞክራሲና አንድነት እንዲጎለብት በውይይቶች፣ በግምገማዎችና በክርክሮች ላይ አባላት ነጻ ሆነው እንዲሳተፉ ያደርጋል፣ የአባላትን ነጻ ተሳትፎ የሚገድቡ ድርጊቶችን እንዳይኖሩ ያደርጋል፣

6. የንዑሳን ኮሚቴዎችን እንቅስቃሴ ይከታተላል፣ አመራር ይሰጣል፣
7. የብልፅግና ቤተሰብ አፈፃፀምን ይከታተላል። በውይይቱ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮችን በመለየት እንዲሰራበት ያደርጋል። ፈጣንና ውጤታማ የግብረ መልስ ሥርዓት እንዲኖር ያደርጋል፣
8. በሥሩ የተደራጁ የብልፅግና ቤተሰብ ጠንካራ ሆነው እንዲንቀሳቀሱ አስፈላጊውን አመራር ይሰጣል።
9. ከብልፅግና ቤተሰብ የሚቀርብለትን እጩ አባላት ወደ ሙሉ አባልነት የማጽደቅ የውሳኔ ሐሳብ መርምሮ ትክክለኛነቱን በማረጋገጥ ለአባላት ኮንፈረንስ በማቅረብ ያፀድቃል።
10. የአባላት መዋጮ በደረሰኝ ሰብስቦ ለሚመለከተው ክፍል ገቢ ያደርጋል።
11. የብልፅግና ህብረት አባላት የፓርቲውን የአሰራሮችና የሥነ-ምግባር ሕጎችን እንዲያከብሩ ያደርጋል፣ የሥነ-ምግባር ጥሰት በሚፈጽሙ አባላት ላይ ለብልፅግና ህብረት የአባላት ኮንፈረንስ በማቅረብ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል።
12. የብልፅግና ህብረት የአባላት ኮንፈረንስ በተሳካ ሁኔታ እንዲካሄድ የሚያስፈልጉ ቅድመ ዝግጅቶን ያከናውናል።
13. የብልፅግና ህብረት የአባላት ኮንፈረንስ ጊዜ ቢያንስ ከአስራ አምስት ቀን በፊት አስቀድሞ በአባላት እንዲታወቅ ይደረጋል።
14. የብልፅግና ህብረት የአባላቱ ኮንፈረንስ አጠቃላይ ሂደት በቃለ-ጉባኤ እንዲያዝ ይደረጋል፣
15. የብልፅግና ህብረት የአባላት ኮንፈረንስ ውሳኔዎችና አቅጣጫዎች በ15 ቀናት ጊዜ ውስጥ የብልፅግና ቤተሰብ በኩል በአባላት እንዲታወቁና ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላሉ፣
16. የብልፅግና ህብረት መረጃዎችና የአባላት ማህደር በአግባቡ ይይዛል፣
17. የብልፅግና ህብረት ኮሚሽን በሚቀርቡ የኢንስፔክሽን ግኝቶች ምክረ ሐሳብና ውሳኔዎች በመቀበል ተገቢነቱ መርምሮ ተግባራዊ ደርጋል፣ አፈጻጸሙንም ያሳውቃል። በአሰራር በተቀመጠው የግንኙነት ጊዜ በጋራ የውይይት መድረክ በመፍጠር ውይይት ያደርጋሉ፣
18. የብልፅግና ህብረት ኮንፈረንስ እና አንድ እርከን ቀጥሎ ላለው የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ወይም ለአመራር ኮሚቴ በየሦስት ወሩ ሪፖርት ያቀርባል።
19. ተጠሪነቱ ለብልፅግና ህብረት ኮንፈረንስና አንድ እርከን ቀጥሎ ላለው ለፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ወይም ለአመራር ኮሚቴ ይሆናል።

## 52.የብልፅግና ህብረት ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት

1. የብልፅግና ህብረት ፖለቲካዊ፣ አደረጃጀትና የባለድርሻ አካላት ስራ ይመራል፣ ያስተባብራል።
2. የብልፅግና ቤተሰብ ፖለቲካዊ አቅም ግንባታ ስራን ይከታተላል፣ በበላይነት ይመራል።
3. የብልፅግና ቤተሰብ ጠንካራ የተደራጁ አሀዶች ሆነው እየተንቀሳቀሱ መሆናቸው ይከታተላል፣ ያረጋግጣል።
4. የአመራር ኮሚቴውንና የብልፅግና ህብረት ኮንፈረንስና የአስቸኳይ ስብሰባዎች በሰብሳቢነት ይመራል።
5. ለብልፅግና ህብረት አመራር ስብሰባ የሚሆን የስራ አፈፃፀም ሪፖርት ያዘጋጃል፣ ያቀርባል።
6. የብልፅግና ህብረት አመራር ኮሚቴ ሪፖርት ያቀርባል፣
7. ተጠሪነቱ ለብልፅግና ህብረት አመራር ኮሚቴ እና በቀበሌ/በከተማ ለፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ይሆናል።

## 53.የብልፅግና ህብረት ፖለቲካ ሥራዎች ሃላፊ ተግባርና ኃላፊነት

1. ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፣
2. የፖለቲካ ስራዎች ንኡስ ኮሚቴ የተቀመጡ ስራዎችን በበላይነት ይመራል ያስተባብራል፡
3. ከህብረቱ ሰብሳቢና ከአካባቢው የፓርቲ ቅ/ጽ/ቤት ፖለቲካ ኃላፊ የሚሰጠውን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።
4. ተጠሪነቱ ህብረቱ ሰብሳቢና ለአንድ ደረጃ ከፍ ላለ ለፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ፖለቲካ ዘርፍ ሃላፊ ይሆናል።

## 54.የብልፅግና ህብረት አደረጃጀት ሥራዎች ኃላፊ ተግባርና ኃላፊነት

1. ለአደረጃጀት ንኡስ ኮሚቴ የተቀመጡ ስራዎችን በበላይነት ይመራል ኮሚቴውን ያስተባብራል።
2. የብልፅግና ህብረት እና የአመራር ኮሚቴ ሰነድ ይይዛል።
3. የብልፅግና ህብረት የአመራር ኮሚቴ ስብሰባና የአባላት ኮንፈረንስ ቃለ ጉባዔ ይይዛል፣
4. ከሰብሳቢው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።
5. ተጠሪነቱ ለሰብሳቢውና ለቀበሌ የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አደረጃጀት ኃላፊ ይሆናል።

## 55. የብልፅግና ህብረት ፋይናንስ ሥራዎች ኃላፊ ተግባርና ኃላፊነት፣

1. ለፋይናንስ ንዑሳን ኮሚቴ የተቀመጡ ሥራዎች በበላይነት ይመራል፣ ኮሚቴውን ያስተባብራል፣
2. የብልፅግና ፓርቲ የአባልነት መዋጮ መቀበያ ህጋዊ ደረሰኝ ከአካባቢው የፓርቲ ቅ/ጽ/ቤት የፋይናንስ ዘርፍ ኃላፊ ይረከባል።
3. ለብልፅግና ቤተሰብ ገንዘብ ያዥ ህጋዊ ደረሰኝ ያሰራጫል፤ ከአባላቱ የተሰበሰበውን የአባልነት መዋጮ ህጋዊ ደረሰኝና የባንክ ስሊፕ በማመሳከር የፓርቲ ቅ/ፅ/ቤት የፋይናንስ ዘርፍ ያወራርዳል፣
4. የልሳነ ብልፅግና መፅሔት ሽያጭ ገንዘብ ወይም የባንክ ስሊፕ ይቀበላል፣ ለአካባቢው የፓርቲ ቅ/ፅ/ቤት የፋይናንስ ዘርፍ ያወራርዳል፣
5. ለብልፅግና ፓርቲ ከፓርቲ ደጋፊ በህጋዊ ደረስኝ መዋጮ ይሰበስባል።

## 56. የፖለቲካ ሥራዎች ንኡስ ኮሚቴ አመራር አባላት አደረጃጀት

1. ንኡስ ኮሚቴው ሦስት የአመራር አባላት ይኖሩታል፣ እነርሱም፡-

   ሀ. የብልፅግና ህብረት ፖለቲካ ሥራዎች ኃላፊ………………….ሰብሳቢ

   ለ. አንድ የብልፅግና ህብረት አመራር ኮሚቴ አባል ……ም/ሰብሳቢ

   ሐ. አንድ /ሁለት/ የብልፅግና ህብረት አመራር ኮሚቴ አባል…. አባል/አባላት/ ይሆናሉ።
2. የንኡስ ኮሚቴው የሚከተሉትን ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፣

   ሀ) እያንዳንዱ አባል ብቁ ፖለቲካዊ ግንዛቤና አቋም ኖሮት ተልዕኮዎቹን በእውቀት ላይ ተመስርቶ ለመፈፀም የሚያስችለው ሁኔታ ላይ እንዲገኝ ተከታታይ ውይይት እንዲኖር ያደርጋል፣

   ለ) የብልፅግና ህብረትና የብልፅግና ቤተሰብ አመራሮች አቅም ግንባታ ስራ እንዲሰራ ያደርጋል፣

   ሐ) የፓርቲው አንድነት፣ ጥራትና ጥንካሬ፣ የፓርቲውን ዕሳቤዎች ለመጠበቅ ሁሉም አባላት ሙሉ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ይሰራል፣

   መ) የብልፅግና ህብረት አባላት የፓርቲ የሥነ-ምግባር ሕጎች እንዲያከብሩ፣ የፓርቲውን ጥንካሬ ከሚጎዱ ማንኛውም ዝንባሌዎችና ድርጊቶች እንዲሁም ከሌብነትና ብልሹ አሰራር ነጻ ሆነው ሌሎችን እንዲያርሙ ያደርጋል፣

   ሠ) በብልፅግና ልሳን ላይ አባላት ውይይት እንዲያካሂዱ ማድረግ።

ረ) የብልፅግና ህብረት ኮንፈረንስ እንዲካሄድ በማድረግ አባላት በኮንፈረንስ መድረኮች ላይ ተገኝተው በሚገባ መሳተፋቸውን /መወያየታቸውንና ግንዛቤ መያዛቸውን ይከታተላል፣

ሰ) የተለያዩ ስልጠናዎችና ሴሚናሮች የመወያያ ርዕሶችንና ሰነዶች በወቅቱ መድረሳቸውን እንዲሁም አወያዮች መሟላታቸውን ይከታተላል፣

ሸ) ተጠሪነቱ ለብልፅግና ህብረት ሰብሳቢና ለቀበሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የፖለቲካ ዘርፍ ኃላፊ ይሆናል።

## 57. የአደረጃጀት ሥራዎች የንኡስ ኮሚቴ አደረጃጀት

1. ንዑስ ኮሚቴው ሦስት የአመራር አባላት ይኖሩታል፣ እነርሱም፡-

ሀ. የብልፅግና ህብረት የአደረጃጀት ሥራዎች ኃላፊ………………….. ሰብሳቢ

ለ. አንድ የብልፅግና ህብረት አመራር ኮሚቴ አባል ………. ምክትል ሰብሳቢ

ሐ. አንድ /ሁለት/ የብልፅግና ህብረት አመራር ኮሚቴ አባል … አባል/አባላት ይሆናሉ።

2. የንኡስ ኮሚቴው የሚከተሉትን ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፣

ሀ. እያንዳንዱ አባል በተልዕኮው ላይ ግልፅ የሆነ፣ ፖለቲካዊ ግንዛቤው ከፍ ያለና ጠንካራ አቋም ያለው፣ በተግባር ራሱ ሰርቶና ተጠቅሞ ለሌሎች በአስተማሪነቱ የሚጠቀስ እንዲሆን ያደርጋል፣

ለ. አባላችን የተደራጀና እንደ አንድ ተልዕኮ ፈፃሚ ኃይል ጠንካራ ተጽዕኖ እያሳረፈና ለውጥ እያመጣ መሆኑን ማረጋገጥ፣

ሐ. አባሉ ተደራጅቶ ወደ ስራ ለመግባትና የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት ያሉበትን ችግሮች በየጊዜው እየገመገመ የመፍትሄ ሃሳብ ያቀርባል፣ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል።

መ) የአደረጃጀትና የአሰራር መመሪያዎች በአባላት ታውቀው ስራ ላይ እንዲውሉ በቂ ግልጽነት ይፈጥራል፣

ሠ) የፓርቲ መተዳደሪያ ደንብና መመሪያዎች በትክክል ስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ችግሮች ካሉ ያስተካክላል።

ረ) የውስጠ-ፓርቲ ዴሞክራሲ እንዲጎለብት በውይይቶች፣ በግምገማዎችና በክርክሮች ላይ አባላት ነጻ ሆነው እንዲሳተፉ ያደርጋል፣ የአባላትን ነጻ ተሳትፎ የሚገድቡ ድርጊቶችን እንዳይኖሩ ያደርጋል፣

ሰ) ከአባላት የሚቀርቡ ቅሬታዎች በዲሲፕሊን መመሪያ መሰረት አጣርቶ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፣

ሸ) ሁሉም አባላት በብልፅግና ቤተሰብ አደረጃጀቶች ውስጥ መደራጀታቸውን ያረጋግጣል፣

ቀ) የአባላት ማህደር በየጊዜው እየተሞላ መያዙን ያረጋግጣል፣ በየ6 ወሩ የውስጠ ፓርቲ ምዘና ማካሄድ በዓመቱ መጨረሻ ላይ ደግሞ የዓመቱ ማጠቃለያ ምዘና በማካሄድ የታደሰ ማህደር መዘጋጀቱን ያረጋግጣል፣ የአባሉ የግል ማህደር ለተፈላጊ ስራ እንዲውል ያደርጋል።

በ) የፓርቲ ደጋፊ ግለሰብና አባላት፣ ዕጩ አባላት ማህደር በአግባቡ መደራጀታቸውን ያረጋግጣል፣

ተ) ተጠሪነቱ የብልፅግና ህብረት ሰብሳቢና ለቀበሌ አደረጃጀት ኮሚቴ ይሆናል፣

## 58.የብልፅግና ህብረት የፋይናንስ ሥራዎች ንኡስ ኮሚቴ

1. ንዑስ ኮሚቴው ሦስት የአመራር አባላት ይኖሩታል፣ እነርሱም፡-

   ሀ. የብልፅግና ህብረት የፋይናንስ ሥራዎች ኃላፊ........................ሰብሳቢ

   ለ. አንድ የብልፅግና ህብረት አመራር ኮሚቴ አባል .......... ምክትል ሰብሳቢ

   ሐ. አንድ የብልፅግና ህብረት አመራር ኮሚቴ አባል .......... አባል ይሆናሉ።

2) የንኡስ ኮሚቴው የሚከተሉትን ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፣

   ሀ) የብልፅግና ህብረት ዓመታዊ የገቢ እቅድ ያዘጋጃል፣ የአባልነት መዋጮ እና ልዩ ልዩ ገቢዎች በአግባቡ ተሰብስቦ በቀበሌ ለፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ገቢ መሆኑን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፣

   ለ) ማንኛውም ገቢዎች በፓርቲ ህጋዊ ደረሰኝ መሰብሰቡን ይከታተላል፣

   መ) ተጠሪነቱ የብልፅግና ህብረት ሰብሳቢና ለቀበሌ ፋይናንስ ኮሚቴ ይሆናል።

## 59.የብልፅግና ህብረት አሰራር

1) የብልፅግና ህብረት የአባላት ኮንፈረንስ በየሶስት ወሩ ይካሄዳል፡

2) የብልፅግና ህብረት **አመራር ኮሚቴ** በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ የሚያካሂዱ ይሆናል፣

3) የብልፅግና ህብረት ንኡሳን ኮሚቴዎች በየወሩ መደበኛ ስብሰባ ያካሂዳል፣

4) የብልፅግና ህብረት ኮንፈረንሱ እና የአመራር ኮሚቴ እንዲሁም የንዑሳን ኮሚቴዎች ምልአተ ጉባዔ አባላት ከግማሽ በላይ /50%+1/ ሲገኙ ይሆናል፣

5) ውሳኔዎች በተባበረ ድምፅ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ/50%+1/ የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል። እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል።

6) የዚህ መመሪያ አንቀጽ 20(4) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የብልፅግና ህብረት አመራር ኮሚቴ አንድ ደረጃ ከፍ ብሎ ካለው የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ ወይም አመራር ኮሚቴ ጋር በሦስት ወር አንድ ጊዜ የስራ ግምገማ ሊያደርጉ ይችላሉ።

## 60. የብልፅግና ቤተሰብ አደረጃጀት

1. የፓርቲ ሙሉና እጩ አባላት ከ11 እስከ 35 የሆኑ በአንድ የብልጸጽግና ቤተሰብ ይደራጃሉ፣
2. **በአንድ** የብልጸጽግና ቤተሰብ በመኖሪያ አካባቢ ወይም በስራ ቦታ የሚደራጁ ብልፅግና ቤተሰብ በሚከተለው መልኩ ይሆናል፣
   ሀ. የመንግስት ሰራተኞች /በክልል፣ በዞን፣ በከተማ፣ በወረዳ/በልዩ ወረዳና በቀበሌ መስሪያ ቤቶች/ የሚሰሩ በተቋም ወይም በየዘርፉ ማለትም ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ አስተዳደራዊ ዘርፎችን መሰረት አድርገው ይደራጃሉ፣
   ለ. በየክልሉ ያሉ የፌደራል ተቋማት አባላት የብልፅግና ቤተሰብ በሚሰሩባቸው ተቋማት የሚደራጁ ይሆናል፣
   ሐ. የመምህራን፣ አስተዳደር ሰራተኞችና የተማሪዎች የብልፅግና ቤተሰብ አመቺ በሆነበት ቦታ /በተቋም፣ በወረዳ፣ በቀበሌ/ ደረጃ ይደራጃል፣
   መ. የሆስፒታል አባላት እንደ አመቺነቱ በሚሰሩበት ተቋም፣ ወረዳ/ቀበሌ ደረጃ ይደራጃሉ፣
   ረ. የገጠር አርብቶና አርሶ አደሮች የብልፅግና ቤተሰብ መንደር/ቀጠናን መሰረት በማድረግ ይደራጃሉ።
   ሰ. በገጠር የተሰማሩ የመንግስት ሰራተኞች የብልፅግና ቤተሰብ የገጠር ባለሙያዎች እና በሌሎች ስራ የተሰማሩትን ባካተተ መልኩ የስራ ቦታ ወይም ቀበሌን መሰረት በማድረግ ይደራጃሉ።
   ሸ. የከተማ ነዋሪዎች የብልፅግና ቤተሰብ የመኖሪያ ቦታን መሰረት በማድረግ በቀበሌ፣ በመንደር፣ በቀጠና ወይም በወረዳ ደረጃ ይደራጃሉ።
   ቀ. የከተማ በኢንተርፕራይዝ የተደራጁ አባላት በተሰማሩበት የስራ ዘርፍ የሚደራጁ ሆኖ ቁጥራቸው አነስተኛ ከሆነ በአቅራቢያቸው ካለ የብልፅግና ቤተሰብ ጋር ይደራጃሉ።
   በ. በክልል መንግስታት ወይም በህዝብ ባለቤትነት የተያዙ የልማት ድርጅቶች የሚገኙ አባላት እንደአመቺነቱ በሚኖሩበት ቀበሌ ወይም በአቅራቢያቸው ባሉ ተቋማት አደረጃጀቶች ውስጥ ታቅፈው የብልፅግና ቤተሰብ ይደራጃሉ።
3. በአንድ ተቋም የሚሰሩ አባላት ቁጥራቸው ከአስራ አንድ በታች ከሆነ ከሌሎች ተቋም ጋር በክላስተር ይደራጃሉ፣

4. በአንድ የስራ ቦታ ወይም መኖሪያ የአባላት ቁጥር ከ35 በላይ ከሆነ ሌላ የብልፅግና ቤተሰብ ይደራጃል፣

5. የብልፅግና ቤተሰብ ተግባራትና ኃላፊነቶች የሚከተሉት ይሆናል፣

ሀ) አባላት በቀበሌያቸው/በወረዳቸው በመስሪያ ቤታቸው ውስጥ በሚካሄዱ ብልፅግናን የሚያረጋግጡና የሰላም ተግባራት ግንባር ቀደም ሆነው እንዲንቀሳቀሱ ማብቃት በዚህ ሂደትም አባላትን በተግባር እንዲገነባ ይደረጋል፣

ለ) በብልፅግና ቤተሰብ ውስጥ የታቀፉትን አባላት በሙሉ በየግላቸው የሚያዘጋጁትን የግል እቅድ ማፅደቅ፣ አፈፃፀሙን መከታተል፣ መደገፍና ውጤቱን መገምገም፣

ሐ) የብልፅግና ቤተሰብ የአባላት ውይይት በወቅቱ እንዲካሄድ በማድረግ እና በሌሎች አጀንዳዎች ላይ የአመራርና የአባላት አቅም ይገነባል፣

መ) አዳዲስ አባላት ምልመላ በመመሪያው መሰረት ብቻ መሆኑ ይከታተላል፣ ችግር ሲያጋጥምም እንዲታረም ያደርጋል፣

ሠ) አባላት በተደራጀ ፓርቲ ህይወት እንዲኖራቸውና የተደራጀ ጠንካራ እንቅስቃሴ እንዲኖራቸው ይደረጋል፣

ረ) የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብ፣ አሰራሮችና መመሪያዎች ስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣

ሰ) የውስጠ-ፓርቲ ዴሞክራሲ፣ አንድነት፣ ጥራትና ጥንካሬ ለማጎልበት የፓርቲውን ዕሳቤዎች ለመጠበቅ ሁሉም አባላት ሙሉ ተሳትፎ ማድረጋቸውን ያረጋግጣል፣

ሸ) የፓርቲው የአሰራሮችና የሥነ-ምግባር ሕጎች እንዲያከብሩ፣ የፓርቲውን ጥንካሬ ከሚጎዱ ማንኛውም ዝንባሌዎችና ድርጊቶች እንዲሁም ከሌብነትና ብልሹ አሰራር ነጻ ሆነው ሌሎችን ማረማቸውን ያረጋግጣል፣

ቀ) የውስጠ-ፓርቲ ዴሞክራሲ እንዲጎለብት በውይይቶች፣ በግምገማዎችና በክርክሮች ላይ አባላት ነጻ ሆነው መሳተፋቸውንና የአባላትን ነጻ ተሳትፎ የሚገድቡ ድርጊቶችን አለመኖራቸውን ያረጋግጣል፣

በ) ከእያንዳንዱ አባል ወርሃዊ መዋጮ በፓርቲ ህጋዊ ደረሰኝ በወቅቱ እንዲሰበሰብና ገቢ እንዲሆን ይከታተላል፣

ተ) በፓርቲና በመንግስት የሚሰጡ የንቅናቄ ሥራዎች ላይ አባላትን በማስተባበር የነቃ ተሳትፎ ያደርጋሉ፣

ቸ) ከአመራር የሚቀርብ ሪፖርት ይገመግማል፣ ያጸድቃል፣

ነ) የብልፅግና ቤተሰብ አመራር ኮሚቴ ይመርጣል።

ኘ) በአባላት ላይ የሚወሰዱ የሥነ-ምግባር ጥሰት የእርምት እርምጃዎች የፓርቲውን የዲሲፕሊን መመሪያ መሰረት መሆኑን ያረጋግጣል፣

ኀ. የፌዴራል ተቋም የብልፅግና ቤተሰብ ተጠሪነታቸው በተቋሙ ላለው ህብረት ይሆናል።

## 61. የብልፅግና ቤተሰብ አመራር ኮሚቴ

1. እያንዳንዱ የብልፅግና ቤተሰብ አራት አባላት ያሉት አመራር ኮሚቴ ይኖረዋል፣ እነዚህም፦

   ሀ. ሰብሳቢ

   ለ. የፖለቲካ ሥራዎች ኃላፊ

   ሐ. የአደረጃጀት ጉዳይ ኃላፊ

   መ. ገንዘብ ያዥ ይሆናሉ

2. ለብልፅግና ቤተሰብ አመራር ኮሚቴ አባላት የመምረጫ መመዘኛዎች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 50(3) ለብልፅግና ህብረት አመራር ኮሚቴ የተቀመጡ ምርጫ መስፈርቶች ይሆናል፣
3. የብልፅግና ቤተሰብ አመራር ምርጫ በየዓመቱ መጀመሪያ ወር በሚካሄድ ስብሰባ ይሆናል፣ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የአመራር መጓደል ካለ በየወሩ በሚደረግ የአባላት መደበኛ ስብሰባ የሚሟሉ ይሆናል።

## 62. የብልፅግና ቤተሰብ አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1. የብልፅግና ቤተሰብ ሰብሳቢና ሌሎች ኃላፊዎች ይመርጣል፣
2. የብልፅግና ቤተሰብ አባላት በተግባርና በአስተሳሰብ ግንባር ቀደም ሆነው በመንቀሳቀስ ላይ መሆናቸውን ይከታተላል፣
3. የፓርቲ መተዳደሪያ ደንብና መመሪያዎችን የብልፅግና ቤተሰብ አባላት እንዲያውቋቸውና በአግባቡ እንዲፈፅሟቸው ያደርጋል፣ አፈፃፀማቸውንም ይቆጣጠራል፣
4. የውስጠ-ፓርቲ ዴሞክራሲ፣ አንድነት፣ ጥራትና ጥንካሬ ለማጎልበት የፓርቲውን ዕሳቤዎች ለመጠበቅ ሁሉም አባላት ሙሉ ተሳትፎ ማድረጋቸውን ያረጋግጣል፣
5. የፓርቲው አሰራሮችና የሥነ-ምግባር ሕጎች እንዲያከብሩ፣ የፓርቲውን ጥንካሬ ከሚጎዱ ማንኛውም ዝንባሌዎችና ድርጊቶች እንዲሁም ከሌብነትና ብልሹ አሰራር ነጻ ሆነው ሌሎችን ማረማቸውን ያረጋግጣል፣

6. የውስጠ-ፓርቲ ዴሞክራሲ እንዲጎለብት በውይይቶች፣ በግምገማዎችና በክርክሮች ላይ አባላት ነጻ ሆነው መሳተፋቸውንና የአባላትን ነጻ ተሳትፎ የሚገድቡ ድርጊቶችን አለመኖራቸውን ያረጋግጣል፣
7. አባላት ተልዕኮዎቻቸውን ከመፈፀም አኳያ ያሉበትን ሁኔታ ይገመግማል፣ እያንዳንዱን አባል ዕቅድ በመገምገም ያፀድቃል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣ ውጤቱን ይገመግማል፣
8. የፓርቲ ደጋፊ አባላት መስፈርቱን አሟልተው ለዕጩነት መመልመላቸውን ያረጋግጣል፣ እጩ አባልነትን እንዲፀድቅ የውሳኔ ሀሳብ ለብልፅግና ህብረት ያቀርባል፣
9. እጩ አባላት የዕጩነት ጊዜያቸውና ተልዕኮአቸውን በብቃት ሲያጠናቅቁ በመገምገም ወደ ሙሉ አባልነት ሊሸጋገሩ ይገባል ብሎ ያመነባቸውን ሙሉ አባልነታቸው እንዲፀድቅላቸው ለብልፅግና ህብረት አመራር ኮሚቴ ሪፖርት ያቀርባል፣
10. የብልፅግና ቤተሰብን የአባላት የውይይትና የግምገማ ፕሮግራሞችን ያዘጋጃል፣ ሲጸድቅ ስራ ላይ ያውላል፣
11. የብልፅግና ቤተሰብ የውይይት ጊዜ ሳይስተጓጎል የሚካሄድበትን ሁኔታ ለመፍጠር ትኩረት ሰጥቶ ይንቀሳቀሳል። የሌሎችን የብልፅግና ቤተሰብ መልካም ተሞክሮ በመቅሰም አባላት እንዲጠቀምበት ያደርጋል፣
12. ለብልፅግና ቤተሰብ ጠቅላላ ስብሰባ በየወሩ ሪፖርት ያቀርባል፣ በየሶስት ወሩ ለብልፅግና ህብረት አመራር ኮሚቴ ይልካል።

63. **የብልፅግና ቤተሰብ ሰብሳቢ የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል።**

ሀ. የብልፅግና ቤተሰብን ስብሰባ በሰብሳቢነት ይመራል፣

ለ. የብልፅግና ቤተሰብን ፖለቲካዊና አደረጃጀት ስራ በበላይነት ያስተባብራል፣

ሐ. የብልፅግና ቤተሰብን በመወከል ከብልፅግና ህብረት አመራር ጋር ይገናኛል፣

መ. የብልፅግና ቤተሰብ ጠንካራ የተደራጀ ሆኖ እንዲንቀሳቀስ የሚያስችል አመራር ይሰጣል፣

ሠ. እያንዳንዱን የብልፅግና ቤተሰብ አባል ፖለቲካዊ እንቅስቃሴውን ጠንካራና ደካማ ጎን በመለየት ድጋፍ እንዲያገኝ ያደርጋል፣

ረ. ስለስራው አፈጻጸም ለብልፅግና ህብረት ሰብሳቢ ሪፖርት ያቀርባል።

64. **የብልፅግና ቤተሰብ ፖለቲካ ሥራዎች ኃላፊ የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል።**

ሀ. የብልፅግና ቤተሰብ እንዲወያይበት ከብልፅግና ህብረት የሚሰጥ አጀንዳ እየተከታተለ ለብልፅግና ቤተሰብ እንዲወያይበት ያደርጋል፣

ለ. ከብልፅግና ህብረት ጋር በመገናኘት አባላት ልሳነ ብልፅግና በየወቅቱ እንዲያገኙ ያደርጋል፣

ሐ. ለብልፅግና ቤተሰብ የአባላት ውይይትን አጀንዳ ይቀርፃል፤ በቤተሰብ አመራር ኮሚቴ ሲፀድቅ በአባላት ውይይት ይደረጋል፤

መ. ስለስራው አፈጻጸም ለብልፅግና ቤተሰብ ሰብሳቢና ለብልፅግና ህብረት የፖለቲካ ኃላፊ ሪፖርት ይልካል።

ሠ. ተጠሪነቱ ለብልፅግና ቤተሰብ ሰብሳቢና ለብልፅግና ህብረት የፖለቲካ ሥራዎች ኃላፊ ይሆናል።

65. **የአደረጃጀት ጉዳይ ኃላፊ የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል።**

ሀ. የብልፅግና ቤተሰብ ጠንካራ ሆኖ እንድትንቀሳቀስ የሚያስችል አመራር ይሰጣል፣

ለ. እያንዳንዱ አባል በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብና መመሪያዎች ላይ ያለውን ግንዛቤ የማጎልበት ስራ ይሰራል፣

ሐ. የብልፅግና ቤተሰብ መረጃዎችና የአባላት ማህደር ይይዛል፣

መ. የብልፅግና ቤተሰብ የአባላት ውይይት፣ ግምገማና ምዘና ቃለ-ጉባዔ ይይዛል፣ በማህደራቸው ላይ ያሰፍራል፣

ሠ. የፓርቲ ደጋፊ አባላት አደረጃጀት እንቅስቃሴ ይከታተላል፣

ረ. ስለስራው አፈጻጸም ለብልፅግና ቤተሰብ ሰብሳቢና ለብልፅግና ህብረት አደረጃጃት ኃላፊ ሪፖርት ያቀርባል፣

ሸ. ተጠሪነቱ ለብልፅግና ቤተሰብ ሰብሳቢና ለብልፅግና ህብረት የአደረጃጀት ሥራዎች ኃላፊ ይሆናል።

66. **የብልፅግና ቤተሰብ ገንዘብ ያዥ የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል።**

ሀ. የአባላትን መዋጮ ያቅዳል፣ በህጋዊ ደረሰኝ በማሰባሰብ ለብልፅግና ህብረት የፋይናንስ ሥራዎች ኃላፊ ገቢ ያደርጋል፣

ለ. የልሳናትና የብልፅግና መፅሔት ሽያጭ ገንዘብ በማሰባሰብ ለብልፅግና ህብረት የፋይናንስ ሥራዎች ኃላፊ ገቢ ያደርጋል፣

ሐ. ሌሎች የፓርቲ ደጋፊ ግለሰብ ገቢዎችን እንደአስፈላጊነቱ አሰባስቦ ገቢ ያደርጋል፣

መ. ውዝፍ መዋጮ ያለባቸውን አባላት በመለየት በመተዳደሪያ ደንቡ እና የዲሲፕሊን መመሪያ መሰረት ውሳኔ እንዲሰጥ ለብልፅግና ቤተሰብ አመራር ኮሚቴ ያቀርባል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣

ሠ. ስለስራው አፈጻጸም ለብልፅግና ቤተሰብ ሰብሳቢና ለብልፅግና ህብረት የፋይናንስ ሥራዎች ንዑስ ኮሚቴ ሪፖርት ያቀርባል፣

ረ. ተጠሪነቱ ለብልፅግና ቤተሰብ ሰብሳቢና ለብልፅግና ህብረት ፋይናንስ ሥራዎች ንዑስ ኮሚቴ ይሆናል፣

## 67. የብልፅግና ቤተሰብ አሰራር

1. በየወሩ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፣
2. **የብልፅግና ቤተሰብ** ስብሰባ የሚካሄደው ከአባላቱ ከግማሽ በላይ ከተገኙ ይሆናል፣
3. **የብልፅግና ቤተሰብ** አመራር ኮሚቴው በየ15 ቀኑ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፣
4. **የብልፅግና ቤተሰብ** የአመራር ኮሚቴ ምልአተ ጉባዔ አባላት ከግማሽ በላይ /50%+1/ ሲገኙ ይሆናል፣
5. **የብልፅግና ቤተሰብ** የአመራር ኮሚቴ ውሳኔዎች በተባበረ ድምፅ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50%+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል። እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል።

## 68. ሁለት ኃላፊነት መያዝ የተከለከለ ስለመሆኑ

1. ለብልፅግና ቤተሰብ አመራር ኮሚቴ የተመረጠው አመራር የብልፅግና ህብረት አመራር በአንድ ጊዜ ሊሆን አይችልም።
2. ለብልፅግና ህብረት አመራር ኮሚቴ የተመረጠው አመራር የብልፅግና የቤተሰብ አመራር በአንድ ጊዜ ሊሆን አይችልም።

## 69. የፓርቲ ደጋፊ አባላት አደረጃጀት

1) ለፓርቲ አባልነት የተመለመሉ ደጋፊ አባላት የተፈጠር አደረጃጀት ነው።
2) አደረጃጀቱን የሚመሩ የአመራር ኮሚቴ አባላት ከመካከላቸው በመደበኛ ሥራቸው ግንባር ቀደምና ለሌሎች አርአያ የሆኑትን ይመረጣሉ፤ ኮሚቴው አራት አባላት ይኖሩታል።
3) ኮሚቴው የራሱ ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ፣ ፀሃፊና አንድ አባል ይኖረዋል።

## 70. የፓርቲ ደጋፊ አባላት አደረጃጀት ተግባርና ኃላፊነት

1) የፓርቲ ደጋፊ አባላት ማመልከቻ ይቀበላል፣ ያደራጃል፤

2) የሁሉም ደጋፊ አባላት ማህደርን አደራጅቶ ይይዛል፣

3) የፓርቲ ደጋፊ አባላትን የፖለቲካ አቅም ግንባታ ሥልጠና ይሰጣል፤

4) በተለያዩ አጀንዳዎች ላይ መደበኛ ውይይት ያደርጋሉ፣ የአመለካከት ብዥታ ሲፈጠር ለአካባቢያቸው ብልፅግና ፓርቲ ቅ/ጽ/ቤት ወይም የብልፅግና ህብረት በማቅረብ ማብራሪያ እንዲሰጥ ያደርጋሉ፣

5) በፓርቲና በመንግስት የንቅናቄ ሥራዎች ላይ የነቃ ተሳትፎ ያደርጋሉ፣

6) የፓርቲ ደጋፊ አባላት ለስድስት ወራት የውስጠ-ፓርቲ ተልዕኮ በመስጠት፣ በመቀበልና በመገምገም አቅማቸው ይገነባል፣

7) የፓርቲ ዕጩ አባልነት የበቁ አባላትን የመለየት ተግባር በማከናወን ለአካባቢው የብልፅግና ፓርቲ ቅ/ጽ/ቤት ወይም የብልፅግና ህብረት ያቀርባል።

8) የፓርቲ ደጋፊ አባላት አደረጃጀት ተጠሪነቱ በአካባቢው ላለው የብልጽግና ፓርቲ ቅ/ጽ/ቤት ወይም አደረጃጀት ይሆናል።

## 71. የፓርቲ ደጋፊ አባላት አደረጃጀት አሰራር

1. በየወሩ መደበኛ ስብሰባ ይኖረዋል፣
2. የፓርቲ ደጋፊ አባላት ውይይት የሚካሄደው ከአባላቱ ከግማሽ በላይ ከተገኙ ይሆናል፣
3. የፓርቲ ደጋፊ አባላት አደረጃጀት አመራር ኮሚቴው በየ15 ቀኑ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል
4. የፓርቲ ደጋፊ አባላት አደረጃጀት የአመራር ኮሚቴ ምልአተ ጉባዔ አባላት ከግማሽ በላይ /50%+1/ ሲገኙ ይሆናል፣
5. የፓርቲ ደጋፊ አባላት አደረጃጀት የአመራር ኮሚቴ ውሳኔዎች በተባበረ ድምፅ የሚፀድቁ ሆኖ ድምፅ መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በ50%+1 የተደገፈ ሀሳብ የአካሉ ውሳኔ ሆኖ ይፀድቃል። እኩል ድምፅ ከመጣ ሰብሳቢው የደገፈው ሀሳብ ፀዳቂ ይሆናል።

## 72. የፓርቲ ደጋፊ ግለሰቦች አደረጃጀት

1) ከመኖሪያ አከባቢ ወይም በስራ ቦታ ፓርቲዉን በእዉቀት፣ በገንዘብና በጉልበት መደገፍ የሚፈልጉ ፈቃደኛ የሆኑ ግለሰቦች በፓርቲ ደጋፊዎች ቡድን በፍላጎትና በመግባባት የሚመሰረት ይሆናል፣

2) እያንዳንዱ ደጋፊ ለመሆን ፍቃደኝነቱን ያረጋገጠ ግለሰብ ከሚቀራረቡትና ከሚስማሙት ሰዎች ጋር እንዲደራጅ ይደረጋል፣

3) የደጋፊዎች ቡድን በተደራጁ የደጋፊዉ ቡድን አባላት በተመረጠ፣ ተቀባይነትና የተግባር መሪነቱ የተረጋገጠ መሪ የሚመራ ይሆናል።

4) የደጋፊ አባል አደረጃጀት አባላት በተደራጁበት የብልፅግና ቤተሰብ ስር ዝርዝር ማህደራቸው በብልፅግና ቤተሰብ ይቀመጣል። በየጊዜው ይታደሳል፣

5) የፓርቲ ደጋፊ አደረጃጀት በፓርቲ ብልፅግና ቤተሰብ የቅርብ ክትትልና ድጋፍ የሚደረግለት ይሆናል።

## 73. የፓርቲ ደጋፊ ግለሰቦች አደረጃጀት ተግባርና ኃላፊነት

1. የፓርቲው ደጋፊዎች ቡድን አዳዲስና አስፈላጊ የሆኑ ሀሳቦችን የሚያገኙበት መድረክ ሆኖ ያገለግላል፣
2. የፓርቲው ደጋፊዎች ለፓርቲው ሊያቀርቡ የሚፈልጓቸዉ ጉዳዮች፣ አስተያየቶች፣ መስተካከል ያለባቸዉ አመላከከቶችና አሰራሮች፣ ለፓርቲው የሚያቀርቡት ገንቢ ሐሳቦችና ነቀፌታዎች፣ ሲኖሩ የሚያመቻች መድረክ ሆኖ ያገለግላል፣
3. ፓርቲው ከጠቅላላ ህዝብና ምሁራን ጋር የሚኖረውን ግንኙነት የሚያስተሳስር መድረክ ሆኖ ያገለግላል፣
4. በሂደትና በሙሉ ፈቃዳቸው ወደ ፓርቲው የሚቀላቀሉ አዳዲስ አባላት በተለይ ደግሞ ምሁራን፣ ባለሀብቶች፣ ወጣቶችና ሴቶች የደጋፊ አባላት መመልመያ መድረክ ሆኖም ሊያገለግል ይችላል፣
5. ፓርቲው የሚያስፈልገው የእውቀት፣ ጉልበትና የገንዘብ ድጋፍ ተጨማሪ አቅም ሆኖ ያገለግላል።
6. የፓርቲ ደጋፊ ግለሰቦች በደጋፊ አደረጃጀት መታቀፍ ይኖርባቸዋል።

## 74. የፓርቲ ደጋፊ ግለሰቦች አደረጃጀት አሰራር

1. የደጋፊ አባል አደረጃጀት ከተመሰረተ በኋላ የስብሰባና የውይይት ጊዜ፣ ከፓርቲው ያለው ግንኙነት፣ ሌሎችም የሚመለከት አሰራር ራሱ ይወስናል፣
2. የደጋፊ ግለሰቦች አደረጃጀት አባላት በተደራጁበት የብልፅግና ቤተሰብ ስር ዝርዝር ማህደራቸው በብልፅግና ቤተሰብ የአደረጃጀት ኃላፊ ይቀመጣል። በየጊዜው ይታደሳል፣
3. የደጋፊ ግለሰቦች አደረጃጀት ግለሰብ የፓርቲው አባል መሆን በሚፈልጉበት ጊዜ ጥያቄያቸው በቀጥታ በአቅራቢያቸው ለሚገኝ የብልፅግና ቤተሰብ ያቀርባሉ።
4. በሂደት የፓርቲ አባል የመሆን ፍላጎት ካላቸው የፓርቲውን አሰራር ተከትሎ ለአካባቢው የብልፅግና ቤተሰብ ጥያቄ የማቅረብ መብት አላቸው፣
5. የደጋፊ ግለሰቦች አደረጃጀት በተስማሙበት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ስለቡድናቸው የስራ አፈፃፀም ነፃ ሆነው ይወያያሉ። የውይይታቸውን ውጤት ለብልፅግና ቤተሰብ ያቀርባሉ።

# ክፍል አምስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 75. በየክልሉ የሚገኙ የፌዴራል መንግስት ተቋማት አባላት አደረጃጀት

1. የፌዴራል ተቋም ተጠሪነታቸው ቀጥሎ ላለው የተቋማቸው አደረጃጀት ይሆናል
2. በየክልሉ ቅርንጫፍ ያላቸው የፌዴራል ተቋማት አደረጃጀቶች ከአካባቢው ፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አመራር ጋር የሚኖራቸው ዝርዝር የአሰራር ግንኙነት የሚወጣለት ሆኖ በምርጫ፣ የሁሉም ተሳትፎ የሚጠይቅ የንቅናቄ ስራዎች፣ ከፌዴራል የሚወርዱ መወያያ ሰነዶች ከአመራር ጋር በመቀናጀት ይሰራሉ፣ ይሰለጥናሉ፣ይወያያሉ፣ የቋንቋ ችግር ካጋጠመ ደግሞ በመነጋገር መፍትሄ ያስቀምጣሉ።

### 76. በየደረጃው የሚኖር የፓርቲ ኮንፈረንስ ውክልና

በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 17 (5)፣ 28 እና 29 መሰረት በየደረጃው ለሚካሄዱ የፓርቲ ኮንፈረንስ ውክልናና ስብጥር እንደሚከተለው ይሆናል፣

ሀ) ለክልል ኮንፈረንስ እንደ ክልል አባላት ብዛት ከ300 እስከ 1500 አባላት ይሳተፋሉ፤

ለ) በዞን/በዞን ደረጃ የሚታዩ ከተሞች ደረጃ እንደ አባላት ብዛት ከ500 እስከ 1000 አባላት ይሳተፋሉ፤

ሐ) ልዩ ወረዳ 600፤ ወረዳዎችና ከተሞች እንደ አባላት ብዛት ከ300 እስከ 500 አባላት ይሳተፋሉ፤

መ) በቀበሌ ደረጃ እንደ አባሉ ብዛት ከ250 አሰከ 300 ይሳተፋሉ፤

ሠ) የኮንፈረንስ ውክልና የፆታን ተዋፅኦን የጠበቁ መሆን ይኖርባቸዋል።

### 77. መመሪያውን ስለማስፈጸም

ይህ መመሪያ በየደረጃው ያሉ የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና አደረጃጀቶች የመፈጸምና የማስፈጸም ግዴታ አለባቸው።

### 78. ግንዛቤ ስለመፍጠር

በየደረጃው የሚገኙ የፓርቲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና አደረጃጀቶች መመሪያውን ለፓርቲ አመራር፣ አባላትና አካላት ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ ይሰራሉ።

## 79. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

ሀ. ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ልማዳዊ አሰራር ወይም ሕግ በዚህ መመሪያ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

ለ. የብልፅግና ፓርቲ አመራርና አባላት አደረጃጀት፣ አሰራርና ተልዕኮ ጊዜያዊ መመሪያ የካቲት 2012 የወጣው በዚህ መመሪያ ተሽሯል።

## 80. መመሪውን ስለማሻሻል

ይህን መመሪያ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በብልፅግና ምክር ቤት ሊሻሻል ይችላል።

## 81. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በብልፅግና ምክር ቤት ከፀደቀበት **ከነሐሴ** 15 **ቀን** 2017 **ዓ.ም** ጀምሮ የጸና ይሆናል።

ነሐሴ 15 ቀን 2017 ዓ.ም

ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

የብልፅግና ፓርቲ ፕሬዚዳንት